«እግዚአብሔር ጻድቃንን ይወድዳል፤ እግዚአብሔር ስደተኞችን ይቀበላል።»

መዝ.፻፵፭፥፱

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች

፬ መልእክት

፮ ሪፖርታዥ

፱ ቤተ አብርሃም

፲፪ ቃለ መጠይቅ

፲፭ የሕፃናት ዓምድ

፲፯ ትዝብት

፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ





## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ

☎ 011-1553555/ 011-1553442

✉ 80078

አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ

ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ

ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ

የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና ጸሐፊ
ገነት ታደሰ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ

# ቅዱስ ፓትርያርኩ ለሕክምና ወደ ውጭ ሀገር እንደሚሄዱ አስታወቁ

ካሳሁን ለምለሙ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ለሕክምና ወደ ውጭ ሀገር እንደሚሄዱ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ለኢ.ኦ.ተ.ቤ ቴቪ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አስታወቁ፡፡

ቅዱስነታቸው በመግለጫቸው በአስቸጋሪ የጤና ሁኔታ ውስጥ መቆየታቸውን ጠቅሰው የተሻለ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ውጭ ሀገር እንደሚጓዙ ተናግረዋል፡፡ የተለየ ችግር ካልገጠማቸው በስተቀር በተቻለ መጠን ከአንድ ወር ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ሕክምናቸውን አጠናቀው ወደ መንበረ ፓትርክናቸው እንደሚመለሱ የገለጡት ቅዱስነታቸው ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ስለ ሀገርና ስለወገን በመጸለይ ሃይማኖታዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ እንዲቆዩ ጠይቀዋል፡፡

የዐይንና ሌሎች ሕክምናቸውን አጠናቀው ወደ ሀገር ቤት እስኪመለሱ ድረስ አባቶችና ምእመናን በጸሎት እንዲያስቧቸው የጠየቁት ቅዱስነታቸው ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት የቤተ ክርስቲያንን ክብር አስጠብቀው አገልግሎታቸውን በኃላፊነት እንዲወጡ የአደራ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

ቅዱስነታቸው ከሐምሌ ፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የተሻለ ሕክምና ለማግኘት ወደ ውጭ ሀገር ሊሄዱ እንደነበር የተናገሩ ሲሆን ሁኔታቻዎች ባለመመቻቸታቸው መቆየታቸውን በመግለጫው አስረድተዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የጉዞ ሁኔታዎች ስለተስተካከሉ ወደ ውጪ ሀገር ሄደው ሕክምናቸውን አጠናቀው እስኪመለሱ ድረስ ምእመናንና ካህናት ተረጋግተው የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ፍጹም በሆነ መንፈሳዊ ስሜት እንዲያከናውኑ አባታዊ መመሪያ አስተላልፈዋል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት ሚዲያ መምሪያ ቅዱስ አባታችን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ሕክምናቸውን በቶሎ አጠናቀው በመልካም ጤንነት ወደ መንበራቸው እንዲመለሱ መልካም ምኞቱን ይገልጻል፡፡



በጦርነቱ ወቅት የወደመ ሕንፃ ቤተ መቅደስ

# በሩሲያና በዩክሬን መካከል እየተደረገ ባለው ጦርነት በርካታ ሃይማኖታዊ ቅርሶች ላይ ጉዳት መድረሱን ዩኒስኮ አስታወቀ

ካሳሁን ለምለሙ

በሩሲያና ዩክሬን መካከል እየተደረገ ባለው ጦርነት ከ ፪፻ በላይ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ቅርሶች በከፊልና ሙሉ በሙሉ መውደማቸውን ዩኒስኮ ማስታወቁን ኦርቶዶክስ ታይምስ ድረ ገጽ አስነበበ፡፡

ጉዳት ከደረሰባቸው ቅርሶች መካከል ፸ ያህሉ ሃይማኖታዊ ቅርሶች መሆናቸውን ያስነበበው ዘገባው አስረድቶ በተጨማሪም ፴ ታሪካዊ ሕንጻዎች፣፲፰ የባህል ማእከላት፣ ፲፪ ሙዚየሞች እንዲሁም ፯ቤተ መጻሕፍት በከፊልና ሙሉ በሙሉ መውደማቸውንም አስረድቷል፡፡

ጉዳት የደረሰባቸው ቅርሶች አብዛኞዎቹ የሚገኙት በዶኔስክ፣ በካራኪብና በኪብ ግዛቶች ሲሆን በዩክሬን ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ቅርሶች ላይ የሚደረገው ተደጋጋሚ ጥቃት ሊቆም እንደሚገባም ዩኒስኮ ማሳሰቡን ዘገባው ያመለክታል፡፡

የዩኒስኮ ዓለም አቀፍ የቅርስ ማእከል ዋና ዳይሬክተር የሆኑት ላዛሪ ኢልኦሁንዶ አሶሞ ከ፪ በላይ የሚሆኑት የዩክሬን ቅርሶች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መውደማቸውን ተናግረው ከወደሙ ታሪካዊ ቅርሶች መካከል ከ፲፩ኛው እስከ ፲፪ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወይም በሶቬት ኅብረት ዘመን የታነፁ አብያተ መዛግብት እንደሚገኙበት አስረድተዋል፡፡

ዳይሬክተሩ አያይዘውም "በልዩ ጥበብና ዕውቀት የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናትና የዩክሬንን የቀደመ ታሪክ የሚዘክሩ ልዩ የሆነ የጥበብ አሻራ ያረፈባቸው ቅርሶች መውደማቸው በቀላሉ የማይታይ ጉዳይ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አክለውም ዩክሬንና ሩሲያ በሁለቱም በኩል ያሉ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች በጦርነት ወቅት የተለየ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስገድድ ስምምነት በ፲፱፻፶፬ ዓ.ም መፈራረማቸውን አስታውሰዋል፡፡

በሁለቱ ሀገራት መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት ከአራት ወራት በፊት ጀምሮ እየተካሄደ ያለ ጦርነት መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡

# የግቢ ጉባኤ በረከቶቻችን የት ናቸው?

ማኅበረ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዛሬ ላይ በሚታየው በተቀናጀ፣ በተደራጀና ለሁሉም ተደራሽ በሆነ መልኩ የጀመረው በግቢ ጉባኤያት ላይ ተመሥርቶ ነው:: ይህም በመንፈሳዊው አገልግሎት ብዙ ፍሬን እንዲያፈራ ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ እንዲያገለግል ሰፊ ዕድል ፈጥሮለታል:: ማኅበሩ ከመመሠረቱ በፊት ቀደም ዩኒቨርሲቲ በገቡ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች የተወሰኑ መንፈሳዊ አገልግሎቶች የነበሩ ቢሆንም ከግቢ ወጥቶ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ከመሳለም፣ ከማስቀደስ ንግሥ በሚሆንበት ጊዜ በዓሉ ላይ ከመታደም የበለጠ ሰፊ አገልግሎት አልነበረም::

እግዚአብሔር በአንድም በሌላም ይሠራልና የብላቴው የጦር ካምፕ ሥልጠና ምክንያት ሆኖአቸው የተገናኙት የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ከሀገራዊው ተልዕኮ ጎን ለጎን ከመንፈሳዊው በረከት ይካፈሉ ዘንድ ምቹ ጊዜ እና አጋጣሚን ፈጥሮላቸው ነበር:: በብላቴ የጦር ካምፕ የተጀመረውና በኋላም በስደት የኬንያ ድንኳኖች ውስጥ የተጠናከረው ኦርቶዶክሳዊው መንፈሳዊ አገልግሎት የሐዋርያትን አሠረ ፍኖት የተከተለ ወንጌልን የማስፋፋት ትልቅ ራዕይ ይዞ ነበር ወደ ሀገር የተመለሰው::

በብዙዎቹ ‹‹እግዚአብሔር የለም›› የሚለው የኮምዩኒዝም ርዕዮተ ዓለምና አስተሳሰብ በሰፈነበት በዚያ እጅግ ፈታኝ በሆነ ዘመን የእግዚአብሔር የለሾችን ርእዮተ ዓለማዊ ከንቱ ሐሳብ የሞገቱና የአስተሳሰቡን ከንቱነት በግልጽ ያሳዩ ዘንድ በአንድም በሌላም ምክንያት ያስነሣቸው እነዚህ ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ከስደት ከተመለሱም በኋላ በየነበሩባቸው ዩኒቨርስቲዎች መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ይበልጥ አጠናክረው የቤተ ክርስቲያንን ሸክም የሚሸከሙ፣ ሕመሟን የሚታመሙ፣ በፈረሰው የቤተ ክርስቲያን ቅጥር በኩል የሚቆሙ፣ በሁለት በኩል የተሳለ ሰይፍ ሆነው ነበር የወጡት:: ለሥራ በሄዱባቸው አካባቢዎች በተለይም በገጠሪቱ የሀገሪቱ የኢትዮጵያ ግዛቶች የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ከመደገፍ አንፃር በአገልጋይ እጦት የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን በማስከፈት ከሚያገኙት ደሞዝ ቀንሰው ካህናት አገልጋዮችን በመደጎም ስብሐተ እግዚአብሔር እንዲደርስ የዐውደ ምሕረት ጉባኤ እንዲጀመር ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ በየአጥቢያው ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ሰጥተው ነበር::

እውነት ነው እንደጨው በምድር ዳርቻ ሁሉ የተበተኑት የግቢ ጉባኤያት ፍሬዎች በየሄዱበት የዓለም ክፍል ሁሉ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከፍ ብላ እንድትታይ፣ ምእመኑን በስፋት ቃለ እግዚአብሔርን እንዲያገኝ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ሲሰጡ ኖረዋል:: በተመደቡበት የሥራ ዘርፍ ሁሉ በገንዘባቸው በዕውቀታቸው በጊዜያቸው ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ የማኅበረ ቅዱሳንን አገልግሎት በሁለት እጃቸው ደግፈው ይዘው ዛሬ ላይ አድርሰውታል:: እነዚያ የ፴ ዓመታት ጉዞ ውስጥ አሻራቸውን ጥለው ያለፉ ብዙ ታሪክ እና ገድል ያላቸው በርካታ መንፈሳውያን አባላት ስብስብ በመሆኑም ማኅበረ ቅዱሳን እጅግ ዕድለኛ ነው ማለት ይቻላል::

ማኅበሩ ከተመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ የግቢ ጉባኤ የደከመባቸው፣ እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን አውቀው እንዲያገለግሏት አደራ የሰጣቸው፣ በተሠማሩበት የሥራ መስክ ሁሉ ታማኝ እና ውጤታማ ሆነው እንዲገኙ እጅግ የለፋባቸው የግቢ ጉባኤያት ፍሬዎች ለቁጥር የሚያታክቱ ቢሆኑም ዛሬ ላይ በዚያ ልክ አሉ ወይ? ካሉስ የት ናቸው? ምን እየሠሩ ነው? የሚለው ሌላ ብዙ ጥናት የሚያስፈልገው ዐቢይ ጥያቄ ነው:: በመላው ዓለም የማኅበረ ቅዱሳን አባላት የሆኑ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች የሌሉበት ባይኖርም በዚያ ልክ ግን ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ ነው ማለት ያስቸግራል::

በግቢ ጉባኤያት ቆይታ የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ምግብ እየተመገቡ ተኮትኩተው ያደጉ፤ ትምህርታቸውን

ሲጨርሱም በአባቶች ተመርቀው እና አደራ ተቀብለው የወጡትንና የሚወጡትን ወጣቶች ተከታትሎ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲበረቱ፣ በተሠማሩበት የሥራ መስክ ቤተ ክርስቲያንንና ሀገራቸውን በቅንነት እንዲያገለግሉ በማድረግ ረገድ የማኅበሩ ድርሻ የት ድረስ ነው? የሚለውም ሌላ ጥያቄን ያስነሣል። ምክንያቱም ለቊጥር ከሚያታክቱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ልጆች በአገልግሎት በርትተው በሄዱበት ቦታ ታማኝ ሆነው የሚገኙት ጥቂቶች ብቻ ናቸውና።

የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ተልዕኮ ከመፈጸም አንጻር ማኅበሩ እየሄደበት ያለው መንፈሳዊ ትጋት አጠያያቂ ባይሆንም በበርካታ ቊጥር ተመርቀው የሚወጡትን የቤተ ክርስቲያን ልጆች የመከታተል፣ እርስ በርስ የሚገናኙበት፣ አንዱ አንዱን የሚያበረታበት እና ሲጠፋ የሚፈልግበት፣ በተለይ በግቢ ጉባኤ ቆይታቸው የተማሩትንና የተሰጣቸውን መንፈሳዊ ተልእኮ ለመፈጸም የሚተጉበት ተከታታይ መድረኮች ማዘጋጀት ተገቢ ነው። በእርግጥ በተለያዩ ጊዜያት ግቢ ጉባኤያትን የሚያጠናክሩ ብዙ የምክክር፣ የውይይት መድረኮች መዘጋጀታቸው ይታወቃል ሆኖም ከግቢ የወጡ እና በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኙ የግቢ ጉባኤ ዓባላት ቀጣይነት ባለው መልኩ የምክክር እና የውይይት ጉባኤ ማድረግ ይገባል።

ትላንት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በአብነት ትምህርት ቤት አልፈው ሀገርን ያገለገሉ፣ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ስሟ እንዲጠራ ያደረጉ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ከሆኑት ውስጥ ሚዛን የሚደፉት የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነበሩ ዛሬም አሉ። ማኅበረ ቅዱሳንም በዚህ ረገድ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለሀገር ያበረከተው ድርሻ ቀላል አይደለም። ዛሬም ላይ ከአጥቢያ እስከ አህጉረ ስብከት ፤ ከወረዳ እስከ ሚንስቴር መሥሪያ ቤቶች በውጭው ዓለምም ሀገራቸውን ወክለው ታላላቅ ሥራ እየሠሩ ያሉት ግቢ ጉባኤያት ፍሬዎች የሆኑ የማኅበሩ ውጤቶች ናቸው። ሆኖም ማኅበሩ በደከመበት ልክ ሁሉም ውጤታማ ናቸው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር አይቻልም። በመሆኑም የግቢ ጉባኤዎቻችንን የነገ አገልግሎት አቅጣጫ ማስያዝ፣ መገምገም የቤት ሥራዎቻችን ሊሆኑ ይገባል።

ትላንት ከግቢ ጉባኤ ወጥተው ዛሬ በተለያየ የሀገሪቱ የሥልጣን እርከኖች ላይ ያሉ፣ በሀብታቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሚያገልግሉ፣ ባሉበት መስክ ሁሉ እናት ቤተ ክርስቲያናቸውን ያልዘነጉ ዘብ የሚቆሙላት፣ ባጠቃላይ ባሉበት ቦታ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅም ሥራ ይሰሠሩ ዘንድ ታላቅ አደራ እንዳለባቸው የዘነጉትን ማሳሰብ፣ማንቃት አስፈላጊ ወቅቱም የሚጠይቀው ጉዳይ ነው።

ባጠቃላይ ከትላንት እስከ ዛሬ ከግቢ ጉባኤ ተመርቀው፤ የቤተ ክርስቲያንን ዓላማ እና አደራ አንግበው የወጡ ዕንቊ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከቊጥር ባለፈ የት እና በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የሚታወቅበትን የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፤ በምን ዓይነት ሕይወት ውስጥ እንደሚገኙ ማጥናት፣ በተሰማሩበት የሕይወት እና የሥራ መስክ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያገለግሉ ማንቃት፣ አሰባስቦ ማወያየት እና ወቅቱ በሚጠይቀው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማሰማራት ተገቢ ነው እንላለን።

# በቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈጸመ ላለው ሕገ ወጥ ተግባር ተጠያቂው ማን ነው?

*ካሳሁን ለምለሙ*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሀገርና ለሕዝብ ያበረከተችውና እያበረከተች ያለችው አስተዋጽኦ ዘርዝሮ መጨረስ ባይቻልም በተለይ በኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ የማይተካ ድርሻ እንደነበራት ማስታወስ የግድ ነው፡፡ በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ሐዋርያዊት በመሆኗ ሀገራችን አሁን ከደረሰችበት የሥልጣኔና የእድገት ደረጃ ከመድረሷ በፊትና ዘመናዊ የትምህርት ሥርዓት በበቂ ሁኔታ ባልተስፋፋበት ዘመን ብራና ዳምጣ፣ ቀለም በጥብጣና ፊደል ቀርጻ ትምህርትንና ሀገራዊ ሥልጣኔን በማስጀመር ለረጅም ጊዜ በትምህርት ሚኒስቴርነት ስታገለግል ቆይታለች፡፡ በሀገር ላይ እነዚህና መሰል ድርሻ የነበራት ቤተ ክርስቲያን ታዲያ በየዘመናቱ ሀገራችንን የሚያስተዳድሩ ሹማምንቶች ሲበድሏት፣ ክብሯንና መብቷን ሲነጥቁ መቆየታቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ በየዘመናቱ ሀገራችንን ያስተዳደሩ አሁንም እያስተዳደሩ ያሉ የፖለቲካ መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ለሀገርና ለወገን ያበረከተችውን ዘመን የማይሽረውንና ትውልድ የማይረሳውን አስተዋጽኦ ወደ ጎን ትተው ህልውናዋን በእጅጉ ተፈታትነውታል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነገሩ “ወርቅ ላበደረ ጠጠር” ሆኖባት በሠራቻት ሀገራችን ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ስደተኛ ሆና መመልከት እጅግ ያሳዝናል፡፡ ከዚህ ቀደም በየዘመናቱ በነበሩ ፖለቲከኞችና አክራሪ ሃይማኖተኞች ያልተቋረጠ ግፍና መከራ ቢያደርሱባትም ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ የተፈጸመባትና እየተፈጸመባት ያለውን ሕገ ወጥ ተግባር ግን የሚስተካከለው አይገኝም፡፡ በተለይም ከ፳፻፲ ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ በሀገሪቱ ‹‹የፖለቲካ ለውጥ መጣ›› ከተባለ ጊዜ በኋላ አክራሪ ብሔርተኞችም ሆኑ ጽንፈኛ ሃይማኖተኞች ቤተ ክርስቲያንን የቁጭትና የእልህ መወጣጫ አድርገዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ በምእመናን የተገነቡ በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ወድመዋል፤ ብዙ ሺህ ምእመናን ያለበቂ ምክንያት በግፍና በጭካኔ ተገድለዋል፤ የምእመናን ሀብትና ንብረት ተዘረፏል፤ ወድሟልም፤ በርካቶችም ለአካልና ለሥነ ልቡና ጉዳት ተዳርጋዋል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ወልደው ከብደው ሀብትና ንብረት ያፈሩበትን አካባቢያቸውን ጥለው ተሰደዋል፡፡

ይህ አረመኔያዊ የሆነ የሕገ ወጦች ድርጊት እንዲቆምም ምእመናን፣ ቅዱስ ሲኖዶስና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ ለመንግሥት ቢያመለክቱም መንግሥት ለችግሩ አፋጣኝና ዘላቂ የሆነ መፍትሄ ባለመስጠቱ ችግር ፈጣሪዎቹ የልብ ልብ እየተሰማቸው አረመኔያዊ ድርጊታቸውን ጊዜና ቦታ በመምረጥ በቤተ ክርስቲያንና በኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ላይ እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ አክራሪና ሕገ ወጥ የመንግሥት አመራሮች በምእመናን ላይ ከሚያደርሱት መከራ በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያንን ርስት አልባ ለማድረግ ብዙ ርቀት ተጉዘዋል፡፡

ይህ ፋታ የሌለው የምእመናን ልጆቿ ህልውና በእጅጉ ያሳሰባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም መጋቢት ፴ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ባወጣችው መግለጫ መንግሥትና ሌሎች አካላት በቤተ ክርስቲያን፣ በካህናትና በምእመናን ላይ የሚፈጽሙትን ትንኮሳ እንዲያቆሙ ጠይቃለች፡፡ የሀገራችን ዋና ከተማ የሆነችውን አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች መንግሥት በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ እየፈጸመ ያለውን ሕገ ወጥ ድርጊት እንዲያስቆም፣ በእኩይ ድርጊት እየተሳተፉ ያሉ የመንግሥት አመራሮችም ለፍርድ ቀርበው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ስታሳስብም ቆይታለች፡፡ መንግሥትም ይህንን ማሳሰቢያዋን ከግምት በማስገባት ሕግና ሥርዓትን በተገቢው ሁኔታ ባለማስከበሩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት በበንኬ ወረዳ ቤተ ክህነት በጮሻ ቅዱስ ሚካኤል እና ቅዱስ ፋኑኤል ምእመናን ላይ የአካባቢው ጽንፈኛ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ከፍተኛ የሆነ የአካልና የሥነ ልቡና ጉዳት ማድረሳቸውን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል፡፡

የአካባቢው ጽንፈኛ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች የቤተ ክርስቲያንን ሕጋዊ ይዞታ በኃይል ለመንጠቅ ባደረጉት ፀረ ኦርቶዶክስ እንቅስቃሴ “እኔም ናቡቴ ነኝ ርስቴን አሳልፌ አልሰጥም” ባሉ አገልጋዮች ካህናትና ምእመናን ላይ ከፍተኛ በደል ፈጽመዋል፡፡ ‹‹አባቱ ዳኛ ልጅ ቀማኛ›› እንዲሉ ፍትሕ ይሰጣሉ ተብለው የታመነባቸው የአካባቢው የመንግሥት አካላትም ለእውነት ሳይሆን እከተለዋለሁ ብለው ላሰቡት እምነት አድልተው ወንጀለኞችን በሕግ አግባብ ከመጠየቅ ይልቅ በድብደባ የተጎዱ ንጹሐን ኦርቶዶክሳውያንን ሲያንገላቱ፣ ሲያዋክቡና ሲያስሩ እንደነበረ ከዚህ ቀደም በነበረው ዘገባችን መረዳት እንችላለን፡፡ እንደነዚህ ዓይነት መሰል ችግሮች ቶሎ ባለመታረማቸው አክራሪ እስላሞች

በስልጤ ዞን ባሉ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት፣ ምእመናን ላይ በፈጸሙት ከፍተኛ ጥቃት አራት አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ ተቃጥለዋል፡፡ በምእመናኑም ላይ የሕይወት ሕልፈትና የአካል ጉዳት ድርሷል፡፡

ለዘመናት ያፈሩት ሀብት ንብረታቸውም በአንድ ጀምበር መውደሙን የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት በወቅቱ አስታውቆ ነበር፡፡ የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናትም የወንጀሉ ተባባሪዎች በመሆናቸው ሀገረ ስብከቱ ከጥቃቱ ማግስት የደረሰውን ጉዳት ለማጣራት ጥረት ሲያደርግ በመንግሥት አመራሮቹ መከልከሉን ማስታወቁ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ የደረደሰውን ውድመት በማጣራት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረትም የአካባቢው የመንግሥት አመራሮች አስፈላጊውን ትብብር እንዳላደረጉ የፍትሕ ሚኒስቴር ባደረገው ምርመራ ማረጋገጡ የሀገረ ስብከቱን ቅሬታ ይበልጥ አጠናክሮታል፡፡

የስልጤ ዞን የመንግሥት አመራሮች ወንጀለኞችን አሳልፈው ከመስጠት ይልቅ ሃይማኖት ተኮር ወንጀል የፈጸሙ ወንጀለኞችን በመደበቅና ወንጀሉን በማድበስበስ ሥራ ላይ መጠመዳቸውን ሀገረ ስብከቱና የፍትሕ ሚኒስቴር በተግባራዊ ምርመራ አረጋግጠዋል፡፡ አመራሮቹ ወንጀለኞችን ለሕግ አካላት አሳልፈው ከመስጠት ይልቅ በድብደባ የተጎዱ ምእመናንና የወራቤ ዩኒቨርስቲ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎችን በእብሪት የማዋከብና የማሠር ተግባር ሲፈጽሙ ቆይተዋል፡፡ ሀገረ ስብከቱም በወራቤ ዩኒቨርስቲ ኦርቶዶክሳውያን ተማሪዎች ላይ ይፈጸም የነበረው ግፍ እንዲቆም ቅዱስ ሲኖዶስ ለትምህርት ሚኒስቴር ደብዳቤ እንዲጽፍ ምክረ ሐሳብ አቅርቦ በአብያተ ክርስቲያናት፣ በምእመናንና በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሱ የስልጤ ዞን የመንግሥት አመራሮች በሕግ እንዲጠየቁና ለደረሰው ኪሳራ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፍል ቢጠይቅም መንግሥት የወንጀል ድርጊቱን እያጣራን ነው ከማለት ውጭ ተጨባጭ የሆነ ርምጃ መውሰዱን አላስታወቀም፡፡

የመንግሥትን መዋቅር በመጠቀም በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ የተፈጸሙት እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሕገ ወጥ ድርጊቶች ባለሥልጣኖቹ በንቀትና በማን አለብኝነት ተነሣሥተው የቤተ ክርስቲያንን ሕጋዊ ይዞታዎችን ለመንጠቅ እያደረጉ ላሉት ሩጫ ማሳያዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሕገ ወጥ ድርጊት በሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ለነበራት ቤተ ክርስቲያን የሚገባት አልነበረም፡፡ የተደራጁ ሕገ ወጥ ቡድኖች ከሚያደርጉት ወረራ በተጨማሪ "የመንግሥት አካላት ነን" የሚሉ ኃይሎች በቤተ ክርስቲያን ርስት ላይ እየፈጸሟቸው ያሉ ሕገ ወጥ ተግባራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ መጥተዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ ምእመናን በመንግሥት ላይ ያላቸውን ሃይማኖታዊና ሰብአዊ ከለላ እያጡ መጥተዋል፡፡ ይህም በመንግሥታዊ አስተዳደሩ ላይ ያላቸውን አመኔታ እንዲሸረሸር ከማድረጉ በተጨማሪ ሌላ አላስፈላጊ ማኅበራዊ ቀውሶችን ሊያስከትልም ይችላል፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ርስት ለመንጠቅና ለመውረር በሀራችን የተለይዩ አካባቢዎች ሙከራ ይደረጋል፤ ከሙከራ አልፎም በርካታ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች በተደራጁ ጽንፈኛ ቡድኖች ተነጥቀዋል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች ይስተዋል የነበረው የቤተ ክርስቲያን ይዞታ ነጠቃ ተጠናክሮና መልኩን ቀይሮ አዲስ አበባ ከተማ ላይ መከሠቱ ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችን በምን ያህል ከባድ ፈተና ውስጥ መሆኗን አመላካች ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የርስት ነጠቃ ሙከራ ከተደረገባቸው በርካታ አጥቢያዎች መካከል በየካ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር የምትገኘውን ደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን እንመለከታለን፡፡ ደብረ ዕንቊ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን 103,952 ካሬ ሜትር የራሷ የሆነ ሕጋዊ ይዞታ ባለቤት ስትሆን በይዞታዋም አዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እየተገበረች እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር በእንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች፡፡ በተለይ በሀገራችን ብሎም በአፍሪካ በርዝመቱና ውስጣዊ ይዘቱ ልዩ የሆነና ፷፬ ሜትር ቁመት ያለው ቅዱስ መስቀል እየገነባች ቆይታ ግንባታውን ከምድር በላይ ፶፬ ሜትር ከምድር በታች ደግሞ ፱ ሜትር አድርሳው ነበር፡፡ ይህ የመስቀል ፕሮጀክት በአንድ ጊዜ ሃያ አምስት ሺህ ሰው የሚይዝ ዐውደ ምህረት (Anfi theater)፣ የቤተ ክርስቲያን ቁሳዊና መንፈሳዊ ቅርሶች የሚታዩበት ደረጃውን የጠበቀ ሙዚዬም፣ የአብነት ትምህርት ቤት፣ ቤተ መጻሕፍት፣ አእምሮን የሚያድስ መካነ ሐመልማል (Green area)፣ ከሱስና ልማዶች ማገገሚያ ማእከል፣ የጥናትና የምርምር ማእከልና የሱባኤ መያዣ ቦታዎችን ያካተተ ሲሆን ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ገጽታ ግንባታ ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው የደብሩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ይሁን እንጂ የመስቀል ፕሮጀክት ሥራው በቤተ ክርስቲያን ይዞታ ላይ በጥራትና በፍጥነት እየተከናወነ ባለበት ወቅት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን የተለያዩ ትንኮሳዎችን ሲያካሄድ ቆይቷል፡፡ ለአብነትም በቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ይዞታ ላይ አርባ ሜትር ስፋት ያለው መንገድ ለመገንባትና የተለያዩ መንግሥታዊ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ በማሽን የታገዘ ቁፋሮን ጨምሮ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተለያዩ ሁከትና ብጥብጥ ሲፈጥር መቆየቱን የደብሩ ዋና አስተዳዳሪ መልአከ ሰላም ነቢየ ልዑል ጌጡ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ አስረድተዋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ይዞታ ላይ ይህ ሁሉ ሕገ ወጥ ድርጊት ሲከናወን ቤተ ክርስቲያን ነገሩን በትዕግሥት ከማየት ውጭ የወሰደችው ርምጃ እንዳልነበርም ገልጠዋል፡፡

ጉዳዩ የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት የሚጋፋ እየሆነ

ሲመጣ ግን የቤተ ክርስቲያንን መብት ማስጠበቅ ሃይማኖታዊ ግዴታ በመሆኑ የሰላም አምባሳደር የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ከአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ጋር መወያየት ብትፈልግም ባለሥልጣን መሥሪያቤቱ ግን ሰላማዊ የውይይት መንገዶችን ሁሉ ዘግቶ ከሕገ ወጥ ተግባሩ ባለመመለሱ በሰላማዊ መንገድ ያልተፈታውን ችግር በሕግ አግባብ መፍትሔ እንዲያገኝ ቤተ ክርስቲያን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርባ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን በፍርድ ቤት በመክሰስ ለወራት ስትከራከር መቆየቷን ዋና አስተዳዳሪው አክለው ገልጠዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን በሕጋዊ ይዞታዋ ላይ እየፈጸመባት ያለውን ሕገ ወጥ ድርጊት እንዲያቆም ለፍርድ ቤቱ ባቀረበችው አቤቱታ መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ፲፮ ፍትሐ ብሔር ችሎት ሰኔ ፳፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል፡፡ በዚህ መሠረት ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ባለ ሥልጣን መሥሪያ ቤት በየካ ወረዳ ቤተ ክህነት በምትገኘው ደብረ ዕንቍ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ይዞታ ላይ የሚያካሄደውን የግንባታ ሥራ፣ የሁከትና ብጥብጥ ተግባር እንዲያቆም ፍርድ ቤቱ መመሪያ ሰጥቷል፡፡

በተሰጠው መመሪያ መሠረትም የግንባታ ሥራውና ሁከትና ብጥብጡ ቢወገድም የመስቀል ሥራ ፕሮጀክቱን ግን እስካሁን ድረስ ሥራው እንዳልተጀመረ አስተዳዳሪው አስረድተዋል፡፡ የመስቀል ፕሮጀክት ሥራው ካቆመበት እንዳይቀጥል ከላይ በመጣ ትዕዛዝ መቆሙን የጠቀሱት ዋና አስተዳዳሪው ምንም ቢፈጠር የመስቀሉ ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት እንደሚጀምር ያላቸውን እምነት ገልጠዋል፡፡ የመስቀል ፕሮጀክት ሥራው እንዲጠናቀቅ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያንና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እስካሁን ድረስ ያደረጉት የነበረውን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ዋና አስተዳዳሪው ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በዚህ ወቅት የመንግሥት አመራሮች በቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች ላይ የሚፈጽሙትን ሕገ ወጥ ድርጊት እንዲያቆሙ ቅዱስ ሲኖዶስ በተለያየ ጊዜ በመግለጫ ጠይቋል፡፡ ከቅዱስ ሲኖዶስ በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያንን ክብርና ልዕልና ዝቅ ለማድረግ እየተፈጸመ ያለው እኩይ ድርጊት እንዲቆም በቅርቡ ምሥረታውን ያከናወነው የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አስተዳዳሪዎች፣ ካህናትና ሠራተኞች አንድነት መሠረታዊ የሠራተኞች ማኅበር በመግለጫ ጠይቋል፡፡ በመግለጫውም ቤተ ክርስቲያንን የማግለል፣ የመተንኮስ፣ ክብሯንና ልዕልናዋን ዝቅ የማድረግ ሙከራ በአስቸኳይ እንዲቆም መንግሥትን የጠየቀ ሲሆን የቤተ ክርስቲያንን ክብርና መብት በማስጠበቅ ዙሪያም ቅዱስ ሲኖዶስ መሬት ላይ የወረደ ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅበት ማኅበሩ አሳስቦ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን በታሪክ አጋጥሟቸው የማያውቅ መከራ ሊገጥማቸው እንደሚችል ገልጧል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ቀደም ውስብስብ ችግሮችን ተጋፍጣ በጥበብና በአባቶች ዕውቀት ማለፍ ብትችልም ከዛሬ አራት ዓመታት ወዲህ እያለፈችበት ያለው መከራ ግን እጅግ ትዕግሥትን የሚፈታተንና የቤተ ክርስቲያንን ህልውና የሚያሰጋ ነው፡፡ የፖለቲካ ሰዎች፣ አክራሪ ብሔርተኞችና ፅንፈኛ ሃይማኖተኞች እያደረሱባት ያለው መከራ እጅግ የከፋ ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አንድነትና ክብር ተጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ የዚህ ዘመን ትውልድ ለነገ የማይባል የተቀናጀና የተደራጀ ሥራ ይጠብቀዋል፡፡ በዚህ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት እንድትሰጥ የውጭና የውስጥ ችግሮቿን መቅረፍ የመጀመሪያው ርምጃ ሊሆን ይገባል፡፡

የቤተ ክርስቲያንን የውጭ ጠላቶች ለመታገል ውስጣዊ አንድነቷን መጠበቅና መንፈሳዊነትንና የአገልግሎት ብቃትን መሠረት ያደረገ አገልጋይ ትውልድን መፍጠርም ተገቢ ነው። አገልጋዮች ከግላዊነትና ከድሏዊነት ተላቀው መንፈሳዊ አገልግሎትን ብቻ ማዕከል አድርገው በአገልግሎታቸው ቤተ ክርስቲያንን እንዲጠቅሙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የዘመነና የተሳለጠ አገልግሎት ካላትና ብልሹ የሆነውን ውስጣዊ አሠራሯን ካስተካከለች የተዳከመው ውስጣዊ አንድነት ይመለሳል፡፡ ይህም ትውልዱ ለቤተ ክርስቲያን የሚኖረው ፍቅርና ተቆርቋሪነት ስለሚጨምር በመንግሥትም ሆነ በጽንፈኞች የሚደርስባትን መከራ ለመከላከል ኃይልና ብርታትን ታገኛለች፡፡

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ የጥፋት እጃቸውን የሚዘረጉ አካላትን ለመከላከል ለሃይማኖቱ የሚቆረቆር፣ የነቃ የበቃና የተደራጀ፣ ሃይማኖቱንና ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ የሚያውቅ ትውልድ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ ቅድሚያ ከራሱ በላይ ለቤተ ክርስቲያን ክብርና መብት የሚታገል፤ አለፍ ሲልም የሚፈጸምባትን በደል እስከሚመለከታቸው ዓለም አቀፍ ተቋማት ድረስ ጉዳዩን ወስዶ ድምጽ የሚሆንላትና ሁሉን አቀፍ ዋስ ጠበቃ የሚሆናት ትውልድ ማፍራት የቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ሥራዋ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ደግሞ በምክክርና በትምህርት የሚመጣ ጉዳይ ነው፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የነገ ተተኪዎቿ ከሆኑት ወጣቶች ጋር ተቀራርባ በመሥራት፣ በማደራጀትና እየደረሰባት ባለው መከራ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር የመጣባትን የመከራ ዘመን ማሳጠር ትችላለች፡፡ ሀገራችንና ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን እግዚአብሔር ይጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡

# ዘመናቸውን ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሰጡ እውነተኛ አባት

ካሳሁን ለምለሙ

ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥነ ጥበብና የኪነ ሕንጻ ጥበብ መነሻ፣የዕውቀት ማኅደር እንዲሁም የሊቃውንት መፍለቂያ መሆኗ ይታወቃል። በርካታ ሊቃውንትን ያፈራችው ቤተ ክርስቲያን ከራሷ አልፋ ለሀገራችን በተለያዩ ዘርፎች አይተኬ ሚና ተጫውታለች፡፡ ከብዙ በጥቂቱ ብራና ዳምጣ፣ቀለም በጥብጣ በዕር ቀርጻ ትውልድን ፊደል ያስቆጠረች እንዲሁም ግበረ ገብን ያስተማረች ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡



መጋቤ ምሥጢር ዶ/ር ኅሩይ ኤርምያስ

ዛሬም ድረስ አስተምራ ለቁምነገር ያበቃቻቸው ሊቃውንት በመላው ዓለም የምእመናን የወንጌል ጥም እያረኩ እና የቤተ ክርስቲያንና የሀገርን ባህልና ዕሴት እያስተዋወቁ ይገኛሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያንን በተለያየ ዘርፍ ካገለገሉ ሊቃውንት መካከል ደግሞ መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኅሩይ ኤርምያስ አንዱ ናቸው፡፡ የእኒህ አባት ትውልድና እድገት አዲስ አበባ ከተማ ጎፋ ገብርኤል አካባቢ ሲሆን ለመንፈሳዊ ትምህርት ካላቸው ፍቅር የተነሣ መንፈሳዊ ትምህርት ለመማር ከትውልድ አካባቢያቸው ከአዲስ አበባ ርቀው ሄደው የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርቶችን ተዘዋውረው ከቀሰሙ በኋላ በቅኔና በትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት ተመርቀዋል፡፡ ከዚያ ኋላም በደብረ ጽላልሽ ኢቲሳ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም ወንበር ዘርግተው ቅኔ ሲያስተምሩ ቆይተዋል። በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከትም በተለያዩ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ተዘዋውረው በዋና ጸሐፊነትና በተለያዩ ኃላፊነቶች ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን አገልግለዋል። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ በቆዩባቸው ዓመታት ላፍቶ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፣ መካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ወይብላ ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን የማይደበዝዝ አሻራቸውን ያስቀመጡባቸው አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡

ከሀገር ውስጥ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው በተጨማሪ በውጭ ሀገር በተለይ በጀርመን በአገልግሎት በቆዩበት ወቅት ምእመናንን በበይነ መረብ ቅኔ ያስተምሩ ነበር። በውጭው ዓለም የቅኔ ትምህርትን በበይነ መረብ ማስተማራቸው የመጀመሪያውና ለሌሎች አባቶች ምሳሌ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል፡፡ በወቅቱ ከበይነ መረብም ሆነ ከዐውደ ምሕረት ምእመናን ለሚያነሷቸው ሃይማኖታዊ ጥያቄዎች ሁሉ በቂ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

የተለያዩ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ይዘት ያላቸው መጻሕሐፍትን ጽፈዋል፤ ተርጉመዋል፤ እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ መጻሕፍትን ለበርካታ አብያተ ክርስቲያናት በስጦታ አበርክተዋል። መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኅሩይ ኤርምያስ አገልግሎት ከጀመሩ ሳይጨርሱ የማያርፉ አባት መሆናቸው ይነገርላቸዋል፡፡ ከፍተኛ የሆነ የንባብና የያዙትን ሥራ በትዕግሥት የመጨረስ ልምዳቸው መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ውጤታማ እንዳደረገው ይነገራል። ባለ ራዕይ አባት በመሆናቸው ከይሆናል ነውን የሚያስቀድሙና በሚሠሩት ሥራ ሁሉ እጅግ ውጤታማ የሆኑ ናቸው፡፡ በዘመናዊ ትምህርት እስከ ሶስተኛ ዲግሪ (ፒኤች ዲ) ድረስ የዘለቁ ሲሆን ካላቸው ዕውቀትና ከአስመዘገቡት ከፍተኛ ውጤት የተነሣ በታዋቂ የውጭ ሀገር ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የማስተማር እድል ቢኖራቸውም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት አስቀድመዋል፡፡ ይህ መልካም ተግባራቸውና ቤተ ክርስቲያንን ያለ ወርኃዊ ደምወዝ ማገልገላቸው ለቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ተቆርቋሪና አርቆ አሳቢ አባት

መሆናቸውን አመላካች ነው፡፡ በዝግጅት ክፍላችንም የመጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ ኤርምያስ መንፈሳዊ አገልግሎት፣ የትምህርትና የሕይወት ተሞክሮ እጂግ አስተማሪ ሆኖ ስላገኘው የቤተ አብርሃም እንግዳ አድረገን ጋብዘናቸዋል፡፡ ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- እስኪ የልጅነት ጊዜዎ ምን ይመስል እንደነበር ቢነግሩኝ?**

**መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ ኤርምያስ፡-** የተወለድኩት ኅዳር ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ጎፋ ገብርኤል ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው፡፡ አባቴ አቶ ኤርምያስ አድነው ሲባሉ እናቴ ደግሞ ወይዘሮ አልማዝ አለሙ ይባላሉ፡፡ ሁለት ወንድሞችና ሁለት እህቶች አሉኝ፡፡ በልጅነቴ ለነገሮች ደፋር የምባል ዓይነት ልጅ አልነበርኩም፡፡ በአንጻሩ ቤተሰቦቼን በሥራ ሳግዛቸው የሚያገኙትን ደስታ ለማየት እየጓጓሁ ያደኩ ልጅ ነኝ፡፡ ከሌሎች ሰዎች ጋር በቀላሉ የምግባባ ልጅ አልነበርኩም፡፡ ነገር ግን ከቤተሰቦቼ ጋር የነበረኝ ግንኙነትና ተግባቦት እጅግ መልካም ነበር፡፡ በልጅነቴ ለጨዋታ ብዙም የምጓጓ ልጅ ስላልነበርኩ በጓደኞቼ ተጫወት ተብዬ እስካልተጋበዝኩ ድረስ የማልጫወት ነበርኩ፡፡ በልጅነት ጓደኞቼ ግፊት አልፎ አልፎ የተለያዩ ጨዋታዎችን እጫወት የነበረ ሲሆን በመንፈሳዊ ትምህርት ተስቤ ወንጌል ማንበብ ስጀምር ግን ከጨዋታው ይልቅ መሉ በሙሉ ትኩረቴን ወደትምህርቴ አደርግ ነበር፡፡

ትልቅ ልጅ ሆኜም እንኳ ጊዜዬን ከአዲስ አበባ ውጭ በሆኑ ጉባኤ ቤቶችና ገዳማት ውስጥ ሳሳልፍ ለትምህርቴ ቅድሚያ በመስጠት ቤተሰቦቼን ከደብዳቤ ልውውጥ ውጭ በአካል አግኝቻቸው አላውቅም፡፡ ወላጆቼም ይህንን ተረድተው ካሉበት ሆነው ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጉልኝ ነበር፡፡ ትምህርቴን ጠንክሬ እንድማርና የወደድኩትን ነገር ሁሉ እንዳደርግ ሙሉ ፈቃድ ይሰጡኛልም፡፡ እኅቴ አንዳንድ ጊዜ ከዘመናዊ ትምህርቴ ጎን ለጎን መንፈሳዊ ትምህርት መጀመሬ በዓለማዊ (ዘመናዊ) ትምህርቴ የምደክም እየመሰላት አብዝታ ትጨነቅ ነበር፡፡

በሌላ በኩል አባቴ የፈለኩትን እንድማር ያበረታታኝ ነበር፡፡ ቤት ሆኜ ለማጥናት ስፈልግ እንኳን የማጠናበትን ምቹ ሁኔታ ያመቻችሉኝ ነበር፡፡ አሁን ትልቅ ሰው ሆኜም መጻሕፍትን ስጽፍና ስተረጉም ቤተሰቦቼ በሙሉ ከፍተኛ እገዛ ያደርጉልኛል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመንፈሳዊና በዘመናዊ ትምህርት ያሳለፉት ጊዜ ምን ይመስል እንደነበረ ቢያስታውሱኝ?**

**መጋቤ ምስጢር ዶክተር ኀሩይ፡-** መንፈሳዊ ትምህርት መማር የጀመርኩት ገና በአራት ዓመቴ ሲሆን አዲስ አበባ በሚገኘው ጎፋ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ለሦስት ወራት ያህል ፊደል፣አቡጊዳና መልእክተ ዮሐንስን ተምሬያለሁ፡፡ አምስት ዓመት ሲሆነኝ ደግሞ መንፈሳዊ ትመህርት አቋርጨ ዘመናዊ ትምህርትን ከአንደኛ ክፍል ጀመርኩ፡፡ ከዚያም አዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የመንግሥት ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ተምሬአለሁ፡፡ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ እያለሁም ያቋረጥኩትን መንፈሳዊ ትምህርት ቀጠልኩ፡፡ ከዚያም አስራ ሁለተኛ ክፍልን እንዳጠናቀኩ ብዙ ጊዜ ሳላጠፋ ባሕርዳር ወደሚገኘው ሽምብጥ ሚካኤል ገዳም ለትምህርት አቅንቻለሁ፡፡ በወቅቱ መንፈሳዊ ትምህርትን የጀመርኩት በከፍተኛ ጉጉትና ፍላጎት ስለነበረ ትምህርቴን ያለምንም ችግር በፍጥነት ማጠናቀቅ ችያለሁ፡፡ በትምህርቴ ቀለም ገብ የምባል ዓይነት ተማሪ በመሆኔ አብረውኝ ይማሩ ከነበሩ ተማሪዎች ቀድሜ ትምህርቴን የምጨርስበት ሁኔታ ነበረ፡፡ ከነበረኝ መልካም የሆነ የትምህርት አቀባበል የተነሣ ኀሩይ ከሚለው መጠሪያ ስሜ በተጨማሪ ዘለቀ የሚል ቅጽል ስም በጓደኞቼ ተሰጥቶኛል፡፡ በዚህ የተነሣ መንፈሳዊ ትምህርቴን በፍጥነት ለመማርና ለመቀበል እግዚአብሔር ረድቶኛል ብዬ አምናለሁ፡፡

በተጨማሪ የመንፈሳዊ ትምህርት የመጀመሪያ ክፍል ያልኳቸውን ንባብ፣የቃልና የቊጥር ትምህርት፣ ዜማና ቅዳሴ አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በሚገኘው ጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ተምሬያለሁ፡፡ ከዚያም ወደ ባሕር ዳር ሽምብጥ ቅዱስ ሚካኤል የካህናት ማሠልጠኛ በመሄድ የመጸሐፍና የቅኔ ትምህርቴን ተከታትዬ ተመርቄያለሁ፡፡ ትምህርቴን ከጨረስኩ በኋላም በእቲሳ ደብረ ጽላለሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም በቅኔ መምህርነት ተመድቤ አገልግያለሁ፡፡ ቅኔ በማስተምርበት ወቅትም የዜማ ትምህርት እማር ነበር፡፡ ከዚያም በታእካ ነገስት በእታ ለማርያም ገዳም መንፈሳዊ ዕወቅቴን ሊያሳድጉ የሚችሉ አንዳንድ ትምህርቶችን ተምሬያለሁ፡፡ በተጨማሪም በዋናነት በጻሕፍትን በማንበብና ሊቃውንትን በመጠየቅ መንፈሳዊ ዕውቀቴን አሳድጌያለሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመንፈሳዊና በዘመናዊ ትምህርት የገፉ አባት ነዎትና ሁለቱን ትምህርቶች ጎን ለጎን ሲማሩ የነበረው ሂደት ምን ይመስል ነበር?**

**መጋቤ ምሥጢር ዶ/ር ኀሩይ፡-** እኔ በተፈጥሮዬ በትምህርት የማምን ሰው ነኝ፡፡ በዚህም የተነሣ

መንፈሳዊ ትምህርቴን በፍላጎትና በትልቅ ጉጉት ነው የተማርኩት፤ ዘመናዊው ትምህርት መማር ግዴታ መሆኑን ተረድቼም እስከ ዶክትሬት ዲግሪ (ሦስተኛ ዲግሪ) ድረስ ተምሬያለሁ። መንፈሳዊም ሆነ ዘመናዊ ትምህርት መማር ለራስ፣ ለእናት ቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ጠቃሚ መሆኑን በጽኑ የማምን ሰው ነኝ።

መንፈሳዊ ትምህርት መማር ለመኖር (ለሥጋዊ ፍላጎት) በራሱ በቂ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከልጅነቴ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ዘመናዊ ትምህርት የተማረ ሰው የላትም የሚል ቁጭት ያድርብኝ ስለነበረ ከመንፈሳዊ ትምህርቴ ጎን ለጎን ዘመናዊ ትምህርት ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት አድሮብኛል። በማኅበረሰባችን እይታ ሁሉም ካህናትና ለሌሎች የቤተ ክርስቲያናችን አገልጋዮች ዘመናዊ ትምህርት ያልተማሩ ተደርጎ ስለሚታሰብ በዚህ ቁጭት ተነሣሥቼ ለቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ትምህርት ከምሰጣት መንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ በዘመናዊውም የተሻለ ድርሻ እንዲኖረኝ አጥብቄ በመሻቴ ነበር ዘመናዊ ትምህርት የተማርኩት። አባቶቻችን መንፈሳዊ ትምህርቶችን ሁሉ ያለምንም ማስታወሻ በጭንቅላታቸው ይዘው የሚያገለግሉ ቢሆንም አንዳንዶቹ ዘመናዊ ትምህርት ያለመማራቸውና በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተወዳዳሪና ተፎካካሪ ያለመሆናቸው ከማኅበራዊ፣ ከፖለቲካዊና ከኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እየተገለሉ አነስተኛ ግምት ሲሰጣቸው ማየቴ ለእኔ እንቅልፍ የነሳኝ ጉዳይ ሆኗል።

እንደነዚህ ዓይነት ችግሮችን ለመቅረፍ ራሴን ለሌሎች አባቶች አርአያ በማድረግ ዘመናዊ ትምህርት ስማር ቆይቻለሁ። በሚገርም ሁኔታ ዘመናዊ ትምህርት ስማር ከባድ የሚባል ፈተና አልገጠመኝም። ምንአልባትም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብቼ ትምህርቴን ሳላጠናቅቅ ያቋረጥኩበት ጊዜ እንደ ችግር ላየው ካልሆነ በስተቀር። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ስከታተል የነበረውን ትምህርቴን ካቋረጥኩ በኋላም ጀርመን ሀገር ለአገልግሎት የመሄድ እድል ስለገጠመኝ ከሄድኩበት ሀገር በሚገኝ ሀንቡርግ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት እድል ተሰጠኝ። ከዚያም ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጎን ለጎን ትምህርቴን መማር ጀመርኩ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ጀርመን ባለው ሀንቡርግ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ላይ የነበረዎት ቆይታ ምን ይመስል ነበር?**

**መጋቤ ምስጢር ዶክተር ጎሩይ፡-** ከዚህ ቀደም ሀገር ቤት እያለሁ የመጀምሪያ ዲግሪዬን በነገረ መለኮት ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርስቲ አግኝቻለሁ። ሁለተኛ ዲግሪዬን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ፊሎሎጅ (ሥነ ድርሳን) ጀምሬ የነበረ ቢሆንም በግል ምክንያት ጥናታዊ ጽሑፍ እየሠራሁ እያለሁ አቋርጨዋለሁ። የመመረቂያ ጽሑፌንም በአቡነ ቀውስጦስ ገድል ላይ ነበር እየሠራሁ የነበረው። ከዚያ በኋላ ጀርመን ሀገር በሚገኘው ሀንቡርግ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ፊደላት ላይ ሁለተኛ ዲግሪዬን ሠርቼ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር (Ethiopian studies) ትምህርት ክፍል ደግሞ ከዚሁ ዩኒቨርስቲ ሦስተኛ ዲግሪዬን አግኝቻለሁ። ይህ ትምህርት ክፍል በጀርመን በሀንቡርግ ዩኒቨርስቲ 230 ዓመታት በላይ ያስቆጠረና የመጀመሪያ የሚባል ነው። ከአሜሪካ፣ ኢንዲያና ከሌሎች ሀገሮች ስተዲስ የቀደመ ትምህርት ክፍል ነው። በመሆኑም በቅኔ ትምህርት አገባብ ላይ መመረቂያ ጹሑፌን ሰርቼ በከፍተኛ ውጤት ተመርቄያለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በዘመናዊም ሆነ በመንፈሳዊ ትምህርት መድረስ የሚገባዎት ደርጃ ላይ ደርሻለሁ ብለው ያምናሉ?**

**መጋቤ ምስጢር ዶክተር ጎሩይ፡-** እኔ በበኩሌ እስካሁን ድረስ መድረስ ካለብኝ ደርጃ ላይ ደርሻለው ብየ አላምንም። በተለይ በመንፈሳዊ ሕይወት ለነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ ለከዊነ እሳት እስኪደርሱ ድረስ ከትሩፋት ወደ ትሩፋት ሲሸጋገሩ መኖር እንጅ በትምህርት የሚመዘን በሥልጣን የሚለካ አይደለም። ትምህርት ዕውቀት ከትሩፋት ወደ ትሩፋት ለመሻጋገር ድልድይ ሆኖ ያገለግላል እንጅ ብቻውን የመንፈሳዊ ከፍታ ማሳያ ሊሆን አይችልም። በመንፈሳዊ ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ ደረስኩ የሚያስብል ሰፊ ትምህርትና ጥልቅ ዕውቀት አለኝ አልልም፤ይህን ማለቴ ከተማርኩት ያልተማረኩት ካወኩት ያላወኩት ስለሚበዛ ነው እንጂ እግዚአብሔር በቸርነቱ ያደረገልኝን ሁሉ ለመካድ አይደለም። በትምህርቴም ሆነ አጠቃላይ በመንፈሳዊ ሕይወቴ ፍላጎት፣ ትጋት፣ ጥረትና የእግዚአብሔር ርዳታ እዚህ የደረስኩበት ደርጃ እንድደርስ አግዘውኛል። መንፈሳዊም ሆነ ዘመናዊ ትምህርት የተማርኩት በከፍተኛ ፍላጎት፣ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም እንዲሁም ለነገሮች ሁሉ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት መስጠቴ ውጤታማ የሆነ የትምህርት ሕይወት እንዲኖረኝ አግዘውኛል። ትጋት የውጤታማነት አንዱ መንገድ መሆኑን ተረድቼ ዘመናዊ ትምህርት ስማር እንኳ ጎን ለጎን መንፈሳዊ ትምህርት እማር ነበር። መንፈሳዊ ትምህርቴን ጨርሸ ወንበር ዘርግቼ ማስተማር ከጀመርኩ በኋላም እንኳን ጎን ለጎን ሌላ ጉበኤ ቤት ያልተማርኳቸውን ትምህርቶች እቀጽል ነበር። በዚያ ሁኔታም ያልገባኝን ሁሉ ለመረዳት የትምህርት አጋሮቸን እጠይቅ ነበር። እኔ አሁን ያለኝ ዕውቀት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ዕውቀት ደግሞ ሰፊና ጥልቅ በመሆኑ አሁንም ቢሆን ከምርምርና ከትምህርት የምርቅ አይመስለኝም።

# ቤተ ክርስቲያን ትልልቅ ፕሮጀክቶችን የማቀድና የመፈጸም ልምዷን አጠናክራ ልትቀጥል ይገባል

ካሣሁን ለምለሙ

የየኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት፣ሐዋርያዊት፣የሰላምና የልማት ምሳሌ መሆኗ ማንም የሚስማማበት ሀቅ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ የዘወትር አገልግሎቷ የሆነውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለሰው ልጅ ሁሉ ስታደርስ ቆይታለች፡፡ በሠራቻቸው መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሥራዎችም ብዙ ወገኖች ከክፉ ሥራቸው ተመልሰዋል፤ ከአምላካቸው እግዚአብሔር እቅፍ ተለይተው ይባዝኑ የነበሩ የእጁ ድንቅ ሥራዎች ወደ በረቱ ተመልሰዋል፡፡ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ከበረቱ ወጥተው እስካሁን ድረስ የሚባዝኑ የሰው ልጆችንም ጭምር ቤተ ክርስቲያናችን በእናትነት መንፈስ እየጣራች ትገኛለች፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን ከምታካሄደው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ጎን ለጎን ማኅበራዊና መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ የልማት ሥራዎችን ስታከናውን ቆይታለች፡፡ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት አሁንም ድረስ በርካታ የልማት ስራዎችን እያከናወነች ትገኛለች፡፡ ይሁን እንጅ ቤተ ክርስቲያናችን ካላት ያልተነካ ሀብት፣ ታሪካዊነትና ጥንታዊነት አንጻር በስብከተ ወንጌል፣ በማኅበራዊና ሃይማኖታዊ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚጠበቅባትን ያህል ርቀት እንዳልተጓዘች የሚናገሩት በርካቶች ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ባላት ከፍተኛ የሆነ መሬት ሀብት፣የሰው ኃይልና የቁስ ሀብት ልክ የሚጠበቅባትን ያህል ያለመልማቷና የምእመናንን ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ መጨመርና ያሉትን ማጽናት አለመቻሏ ከአሠራር ድክመት፣ ከቸልተኝነትና ከውስጣዊ የአሠራር ብልሹነት የመነጨ መሆኑን ሰው ሁሉ የሚገነዘበው ሀቅ ነው፡፡ በተለያዩ ቦታዎች መጠነኛ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ የልማት ሥራዎች ወይም ፕሮጀክቶች ሲሠሩ የሚታዩ ቢሆንም የሚሠሩት የልማት ሥራዎች የምእመናንን ቁጥር ያላገናዘቡና የአገልግሎት ውስንነት ያለባቸው ሆኖ የታያል፡፡ የሚሰጡት አገልግሎትም የተወሰነና ለተወሰኑ ተገልጋዮች ብቻ ሲሆንም ይስተዋላል፡፡ ይህም በቂና ደርጃውን የጠበቀ አገልግሎት ለተገልጋዩ ለመስጠት ከአኃት አብያተ ክርስቲያናት ልምድና ተሞክሮ ካለመውሰድ የመነጨ ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን አስተባብራ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር የሚጠቅሙ ትልልቅ የልማት ሥራዎችን (ፕሮጀክቶችን) የመፈጸም አቅም ያላት መሆኑ እየታወቀ ተፈጻሚ ባለማድረጓ ግን ሁላችንን ያስቆጨ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህ ወቅት ግን የተለያዩ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር ጥረት የሚያደርጉ አንዳንድ አጥቢያዎችን መመልከት እየተለመደ የመጣ በጎ ተግባር ሲሆን የዚህ በጎ ተግባር ማሳያውና ፈር ቀዳጅ ሊባል የሚችለው ደግሞ የላም በረት ደብረ ፀሐይ አቡነ አረጋዊ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ቅድስት አርሴማ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ከዛሬ ስምንት ዓመታት በፊት የተወጠኑትን ፴፰ ትልልቅ ፕሮጀክቶች የራሱ ሕጋዊ ይዞታ በሆነው ፶፬ ሽህ ካሬ ሜትር ላይ ተግባራዊ እንደሚሆን መስማት ልብን በሐሤት ይሞላል፡፡ ይህም ተግባር ለሌሎች አጥቢያዎች የይቻላልንና የይሆናልን መንፈስን የሚያስተጋባ ነው፡፡ ለፕሮጀክቶቹ ተግባራዊነት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ በቅርቡ ወደ ተግባር እንደሚገባ አዘጋጆቹ ባዘጋጁት መድረክ አሳውቀዋል፡፡ ዝግጅት ክፍላችንም በመርሐ ግብሩ ላይ በተሳተፈበት ወቅት በፕሮጀክቶቹ ዙሪያ ከደብሩ የልማት ኮሚቴ ሒሳብ ሹምና የፕሮጀክት ጥናትና ምርምር ኃላፊ ከሆኑት ከአቶ ይድነቃቸው ተፈራ ጋር አጭር ቆይታ አድርጓል፡፡ ያደርግነውን አጭር ቆይታም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በላምበረት ደብረ ፀሐይ አቡነ አርጋዊ፣አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ቅድስት አርሴማ ቤተ ክርስቲያን የሚተገበሩት በርካታ ፕሮጀክቶች ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው የታቀዱት?**



**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** የላምበረት ደብረ ፀሐይ አቡነ አረጋዊ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስና ቅድስት አርሴማ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተ ፳ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ደብሩ ከተመሠረተ

በኋላ ለአገልግሎትና ለካህናት አገልጋዮች ወርኃዊ ደምወዝ የሚሆን ገቢ ማስገኛ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በቅርቡ ተግባራዊ ይሆናል ተብለው የታሰቡ እጅግ ግዙፍ ፕሮጀክቶች እቅድ ከዛሬ ፰ ዓመታት በፊት ታቀደ፡፡ በወቅቱ ዕቅዱ ሲታቀድ በአጥቢያው ዙሪያ የነበሩ ምእመናን ቁጥር እጅግ አናሳ በመሆኑ አገልግሎቱንና አገልጋዮችን በተፈለገው መጠን መደገፍ አልተቻለም ነበር፡፡ በመሆኑም ደብሩ ባለው አጠቃላይ ሃምሳ ዐራት ሽህ ካሬ ሜትር ሕጋዊ ይዞታ ላይ የተለያዩ ፕሮጀክቶች መሠራታቸው ቤተ ክርስቲያንን፣ አገልገዮችን፣ የአካባቢውን ምእመናንና ሀገርን ሊጠቅሙ ይችላሉ ተብሎ በመታሰቡ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያላቸው ፕሮጀክቶችን ለመተግበር እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው ያለው፡፡

ፕሮጀክቱ ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮችን ለመጥቀም ብቻ ያለመ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን ያላትን ሕጋዊ የመሬት ይዞታ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንድታውል ጭምር የታሳበ ነው፡፡ ፕሮጀክቶቹ ከመንፈሳዊ አገልግሎት በተጨማሪ ማኅበራዊ አገልግሎት ጭምር እንዲሰጡ ታስቦ የተቀረጹ በመሆናቸው ሁሉንም አካላት ተጠቃሚ የሚያደርጉ ናቸው፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- አጠቃላይ በደብሩ ይዞታ ላይ ምን ያህል ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ይሆናሉ?**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** አጠቃላይ ተግባራዊ የሚሆኑት ፕሮጀክቶች ፴፰ ናቸው፡፡ ፕሮጀክቶቹም ሁለት ክፍል ያላቸው ሲሆንየመጀመሪያው ክፍል ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ገቢ በማመንጨት ላይ ትኩረታቸውን ያደረጉ ይሆናሉ፡፡ የፕሮጀክቶቹ አብዛኛው ክፍሎች በመንፈሳዊ አገልግሎት መሠረተ ልማቶች የሚሸፈኑ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ በገቢ ማስገኛ ልማቶች ይሸፈናሉ፡፡ ከፕሮጀክቶቹ መካከል የስብከተ ወንጌል አዳራሽ፣ደረጃቸውን የጠበቁ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ዲጂታል ላይብረሪዎች፣የአስተዳደርና ሰበካ ጉባኤ ቢሮዎች፣ደረጃቸውን የጠበቁ መጸዳጃ ቤቶች፣ የካህናት አባቶች መኖሪያና ግሪን ኤሪያዎች ከአገልግሎት መሠረተ ልማቶች መካከል የሚካተቱ ሲሆን በገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶች ሥር ያሉት ደግሞ ትምህርት ቤቶች፣ወፍጮ ቤቶች፣የዳቦ ማምረቻና ማከፋፋያ፣የንብና ከብት ርባታ፣የጤና ተቋማት እንዲሁም ሌሎች በርካታ ፕሮጀክቶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች በተለይ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዲሰጡ ተደርጎ ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው፡፡ ፕሮጀክቶቹ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ከሚሰጡት ድጋፍ በተጨማሪም የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ከመደገፍ አኳያ ደግሞ የላቀ ድርሻ ይኖራቸዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ በሚሆኑበት ወቅትም ሆነ ከተሠሩ በኋላ የአካባቢው ወጣቶች የሥራ እድል ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ወጣቶች የሥራ ዕድል ከማግኘታቸው በተጨማሪም በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ መነቃቃትን ይፈጥራል፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ በተጠቀሱት ፕሮጀክቶች አማካይነት ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ አቅምም ትፈጥራለች፡፡ አሁን በተጠናው ጥናት መሠረትም አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ወጭ ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ የሚጠይቅ ሲሆን ይህ ግዙፍ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ለብዙዎች መልካም በረከት ይዞ ይመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በፕሮጀክቶቹ ትግበራ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶችና ምክክሮች ካሉ ቢገልጹልን?**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** ፕሮጀክቱ በእቅድ ደርጃ ከተጀመረ ከስምንት ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን ሂደቱም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት፣ ከወረዳ ቤተ ክህነት፣ ከሀገረ ስብከት፣ ከደብሩ ሰበካ ጉባኤ እና ከምእመናን ጋር ተከታተይ ውይይቶች ተደርጎበታል፡፡ ስለፕሮጀክቱ ዓላማና ጥቅም ለምእመናንና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ገለጻ ተደረጎላቸዋል፡፡ የፕሮጀክቱ ተግባራዊነት ረጅም ጊዜ የወሰደው በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ውይይቶች ከምእመናንና አጠቃላይ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመደረጋቸውና የፕሮጀክት ክለሳ በመደረጉ ጭምር ነው፡፡ በተጨማሪም በተለየ ሁኔታ ከአካባቢው ወጣት ማኅበራትና የጥምቀት ተመላሽ ወጣቶች ጋር በፕሮጀክቱ ዙሪያ ተደጋገሚ ውይይቶች ተካሄደዋል፡፡ ከደብሩ የሥራ ኃላፊዎችና ከመንግሥት አካላት ጋርም በተለያዩ ጊዜያት ውይይቶች ነበሩ፡፡ ከመንግሥት ጋር ተደጋገሚ ውይይቶችን ለማድረግ ጥረት ተደርጎ ያልተሳካ ቢሆንም ስለፕሮጀክቱ ዓለማና ጥቅም በመጠኑም ቢሆን ለማስረዳት ጥረት ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል ወጣቶችና አጠቃላይ የደበሩ ምእመናን ጉዳዩን በደንብ እንዲረዱት ከማድረግ አኳያ የደብሩ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች የላቀ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሰበካ ጉባኤው ከልማት ኮሚቴው ጋር በቅርበት እየሠራም ይገኛል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት የኦርቶዶክሳውያን ባለሙያዎች ሚና ምን ሊሆን ይችላል?**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** ፕሮጀክቱ በዋናነት በደብሩ አስተዳደርና በሰበካ ጉባኤው የሚመራ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በጣም ግዙፍ ከመሆኑ የተነሣ ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይልና ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡ ስለሆነም በተለያየ ሙያና ዘርፍ ያሉ ኦርቶደክሳውያን ባለሙያዎች በብዛትና በጥራት ያስፈልጋሉ፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ልጆቿ (ምእመናን) ሀብቶቿ ስለሆኑ እንደየሙያቸውና እንደብቃታቸው በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት የሚሳተፉ ይሆናል፡፡ ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላም ፕሮጀክቶቹን በበላይነት ኃላፊነት ወስዶ የሚመራ የሰው ኃይል ያስፈልጋልና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ደበሩ ያለው ሃምሳ አራት ሽህ ካሬ ሜትር የቆዳ ስፋት ከታቀደው ፴፰ ፕሮጀክቶች ጋር እንዴት ሊጣጣም ይችላል?**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** የደብሩ ይዞታ በበቂ ሁኔታ ለተፈለገው ፕሮጀክት አገልግሎት ላይ መዋል እንደሚችል በባለሙያዎች ተረጋግጧል፡፡ እንደ ቦታው ነባራዊ ሁኔታ ደረጃውንና ይዘቱን ጠብቆ እያንዳንዱ ፕሮጀክት ተግባሪዊ ይሆናል፡፡ ፕሮጀክቶቹ የራሳቸው የሆነ የማስፋፊያና የማሻሻያ ፌዝ (ደርጃ) አላቸው፡፡ ስለሆነም ከቦታው ጥበትና ስፋት ጋር የማይሄዱ ፕሮጀክቶችን የመከለስና የመሻሻል እድልም ይኖራል፡፡ አንደኛው ፕሮጀክት በሌላው ላይ ጫና እንዳያመጣ ተደርጎ የተቀረጸ በመሆኑ ሁሉም ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ቦታ ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ እንዲሁም ፕሮጀክቶቹ ተግባረዊ የሚሆኑት የቤተ ክርስቲያናችንን የገንዘብ አቅም ከግመት ውስጥ ባስገባ መልኩ ይሆናል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ፕሮጀክቶቹ በምን ያህል ጊዜ ሠርቶ ማጠናቀቅ ይቻላል?**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ የታቀዱት ፕሮጀክቶች በጣም በርካቶች ናቸው፡፡ ይህ በመሆኑም ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ ሲሆኑ አንዳንዶቹ አንዱ የሌላውን መጠናቀቅ የሚጠብቁ ይኖራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ከጅምሩ እራሳቸውን ችለው የሚጠናቀቁ ናቸው፡፡ በርካታ ፕሮጀክቶች ግን በአንድ ጊዜ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ የሚመለከተው አካል ፕሮጀክቶቹ እንዲጀመሩ ትእዛዝ ሲሰጥ በቀጥታ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ እያንዳንዱ ፕሮጀክትም የጊዜ ገደብ ተቀምጦለታል:: ካለው ሁኔታ አንጻር በዚህን ያህል ጊዜ ፕሮጀክቶቹን እንጨርሳለን ብለን መወሰን ባንችልም ሁሉም ፕሮጀክቶች ግን በታሰበውና በአጭር ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

ገንዘቡ በጣም ከፍተኛና ከቤተ ክርስቲያን አቅም በላይ ቢሆንም ባለድርሻ አካላት የተሻለ ተሳትፎ ያደርጋሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ ባለድረሻ አካላት ከሚያደርጉት የገንዘብና የቁሳቁስ በድጋፍ ባሻገር አንዳንድ ፕሮጀክቶችን በኃላፊነት ይዘው የሚሠሩ ይሆናል፡፡ በተለይ ምእመናን በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት ከፍተኛ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

ሁሉም አካል የድርሻውን የሚወጣ ከሆነ ፕሮጀክቶቹን በጥራትና በፍጥነት ማጠናቀቅ ይቻላል፡፡ የፕሮጀክቶቹን ወጭ ለመሸፈን የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብራትንና ሌሎች መንገዶችን እንጠቀማለን፡፡ ሌላውና ዋናው ነገር ደግሞ ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን ቀድመን በማጠናቀቅ ገቢ በማያስገኙ የአገልግሎት ፕሮጀክቶች እንዲጠናቀቁ እናደርጋለን፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ከእንደነዚህ ዓይነት ፕሮጀክቶች ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ምን ሊማሩ ይገባል? ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትስ ለፕሮጀክቱ ተግባራዊነት ሊኖራቸው ሚችለው ድርሻ ምንድን ነው?**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** እነዚህን በርካታ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ማድረግ ከቻልን ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ፍላጎትና ትጋት ካለ ከቤተ ክርስቲያናችን አቅም በላይ ሊሆን የሚችል ነገር እንደሌለ ይማራሉ፡፡ ፕሮጀክቱ በቤተ ክርስቲያንና በሀገር ደርጃ ትልቅ ምሳሌ የሚሆን ነው፡፡ እንደሚታወቀው በቤተ ክርስቲያናችን ከዚህ ቀደም የተለመደው ትንንሽ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ ማጠናቀቅ ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት ግን እጅግ ግዙፍና ሌሎች አጥቢያዎችም ከትንንሽ ፕሮጀክቶች ወጥተው ሌሎች ትልልቅ ፕሮጀክቶችን መሞከር እንዳለባቸው ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡ ነገሮች ከባድ ሊመስሉ ይችላሉ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያናችን ከራሷ ባሻገር ለሀገር የሚጠቅሙ ፕሮጀክቶችን ሠርታ ማጠናቀቅ ትችላለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን ካላት ሁለንተናዊ ሀብት አንጻር እነዚህ ፕሮጀቶች መተግበር ምንም ማለት ላይሆን ይችላል፡፡

ካለን ሀብት አንጻርም ገና ልንሠራቸው የሚገቡ በርካታ ነገሮች እንዳሉ ማየት ይቻላል፡፡ በተለይ ምእመናን የሚጠበቅባቸውን ማድረግ ከቻሉ ሁሉንም በተባበረ ክንድ መሥራት እንችላለን፡፡ በዚህ የተነሣ ምእመናን የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡ በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት አጠቢያዎች ከእኛ ልምድና ተሞክሮ ይወስዳሉ፤እኛም ከእነርሱ እንወስዳለን፡፡ በተጨማሪም በተለይ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሚገኙ አጥቢያዎች የገንዘብ፣የቁሳቁስና ሙያዊ እገዛ ያደርጋለሁ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** ፕሮጀክቱ ከመነሻው በበርካታ ፈተናዎች ውስጥ በመቆየቱ ተግባራዊ ሳይሆን ፰ ዓመታትን አሳልፏል፡፡ ፕሮጀክቱ በተለይም የገቢ ማስገኛዎቹ ቀድመው ተግባራዊ የሚሆኑ ከሆነ በቀላሉ ሌሎች ፕሮጀክቶችን ለመተግበር ሰፊ ጊዜ አይወስድብንም፡፡ ስለሆነም በቤተ ክርስቲያንና በሀገር ደርጃ እንደዚህ አይነት ግዙፍ ፕሮጀክትን ከዳር ለማድረስ ቤተ ክርስቲያን፣ ምእመናን አገልጋዮች፣መንግሥትና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የበኩላቸውን ድርሻ ሊያበረክቱ ይገባል፡፡ በተለይ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የቅርብ ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ ከሆኑ በኋላም በትክክል የሚያስተዳድራቸው በቂ የሰው ኃይል ያስፈልጋል፡፡ ሌላው ከዚህ ቀድም በቤተ ክርስቲያን ደርጃ ተሠረተው የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የአስተዳደር ችግሮች ሲስተዋልባቸው ይታያል፡፡ ከዚህ በኋላ ቤተ ክርስቲያናችን የተሳለጠ አስተዳደራዊ መዋቅር ሊኖራት ይገባል እላለሁ፡፡ እንደሚታወቀው ቤተ ክርስቲያናችን በጣም ከፍተኛ የሆነ ሀብት አላት ነገር ግን በብልሹ አሠራር ምክንያት ሀብቷ ሲባክን ይታያል፡፡ በነዚህ ፕሮጀክቶች ላይም ከፍተኛ የሆነ ብክነት እንዳይኖር ታስቦበት ፕሮጀክቶቹ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ የቤተ ክርስቲያናችንን የልማትና ስብከተ ወንጌል አገልግሎት ለማሳለጥ መደጋገፍ ያስፈልጋል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለነበረን ቆይታ እግዚአብሔር ይስጥልን?**

**አቶ ይድነቃቸው ተፈራ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ቅድስት ኢየሉጣና ቅዱስ ቂርቆስ

እህተ ሚካኤል

ልጆች! እንደምን ከረማችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን እኛ በጣም ደኅና ነን፡፡ ክረምት እንዴት ነው? ባለፈው እትማችን ላይ የክረምቱን ጊዜ ዝም ብላችሁ ማሳለፍ እንደሌለባችሁ፤ የሚቀጥለው ዓመት ትምህርታችንሁን እንድታጠኑ እንዱም የተለያዩ መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብ ፤ቤተ ክርስቲያን በመሄድ መንፈሳዊ ትምህርት እንድትማሩ ነግረናችሁ ነበር፡፡ የመከርናችሁን ምክር ተግባራዊ እንዳደረጋችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በርቱ እሺ ጎበዞች!



ልጆች! በዚህኛው እትማችን የምንነግራችሁ ስለ ቅዱስ ገብርኤል ፣ቅድስት እየሉጣና፣ ልጇ ቅዱስ ቂርቆስ ነው፡፡ በጥሞና ትከታተሉን ዘንድ ግብዣችን ነው፡፡

ልጆች! ሐምሌ ፲፱ ቀን በየዓመቱ ቅድስት ኢየሉጣና የልጇ ቅዱስ ቂርቆስ ሰማዕትነትን የተቀበሉበት በዓል ይከበራል፡፡ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከፈላ ውኃ ያዳነበት ቀን ነውና በቤተ ክርስቲያናችን የእነዚህ ቅዱሳን በዓል በታላቅ ድምቀት ይከበራል፡፡

ልጆች! የሰማዕጡ የቅዱስ ቂርቆስ እናት ቅድስት ኢየሉጣ በሮም አንጌቤን በሚባል ሀገር ትኖር የነበረች በክርስትና ሃይማኖቷ ጽናት የተመሰከረላት እጅግ ደግ ሴት ነበረች፡፡ ለእርስዋም እጅግ ተወዳጅ የሆነ በሥነ ምግባር ታንጾ ያደገ ቂርቆስ የሚባል ልጅ ነበራት፡፡ እነርሱ በሚኖሩበት ሀገር እለእስክንድሮስ የሚባል እግዚአብሔርን ማያውቅ አረማዊ መኮንን ነበረ፡፡ ይህ አረማዊ መኮንን እግዚአብሔርን የማይፈራ፣ ክርስቲያኖችንም በእጅጉ የሚያስቃይ ክፉ ስለነበረ ልጅዋን ቂርቆስን ይዛ ጠርሴስ ወደምትባል ሀገር ተሰደደች፡፡

መኮንኑም እነርሱ ከተሰደዱበት ሀገር ገብቶ ክርስቲያኖችን ጣዖት እንዲያመልኩ፣ ሃይማኖታቸውን እንዲለውጡ፣ እግዚአብሔርንም እንዲክዱ እጅግ ያሰቃያቸው ነበረ፡፡ የንጉሡ ወታደሮችም በሀገሩ ውስጥ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች በማሳደድ ቀንና ሌሊት እረፍት ነሱአቸው፡፡ ቅድስት ኢየሉጣንና ሕፃኑ ቂርቆስንም እግዚአብሔርን እንዲክዱና ለጣዖት እንዲሰግዱ አስገደዷቸው፡፡ ለጣዖት ካልሰገዱም በሌሎቹ ክርስቲያኖች ላይ እንዳደረጉት ስቃይ እንደሚያበዙባቸው ጭምር አስጠነቀቁአቸው፡፡ እነርሱ ግን ትእዛዛቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ሃይማኖታቸውን እንደማይቀይሩ፣ለጣዖት እንደማይሰግዱ በድፍረት ነገሩአቸው፡፡ የንጉሡ ወታደሮችም በጋሉ ብረቶች ሰውነታቸውን እየወጉ፣ እየበሳሱ ያሰቃዩአቸው

ነበረ፡፡ በዓይንና በአፍንጫቸው ውስጥ ጨውና ሰናፍጭ በመጨመር ስቃያቸው እንዲጨምር ያደርጓቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን የጋለውን ብረት እያቀዘቀዘ ስቃያቸውን ያቀልላቸው ነበር፡፡

በዚህም ቅድስት ኢየሉጣና ቅዱስ ቂርቆስ በሃይማኖታቸው ጸንተው ስለተገኙ ንጉሡ በገመድ አሠራቸው፡፡ ይባስ ብሎም የራስ ጸጉራቸውን ከቆዳቸው ጋር ካስላጫቸው በኋላ እሳት ቁስላቸውን እሳት እያነደደ ለኮሰባቸው፡፡ ያም አልበቃ ብሎት ከትከሻቸው እስከ እግራቸው በሚደርስ በችንካር ቸነከራቸው፡፡ እነርሱ ግን በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት በማጽናታቸው ንጉሡ በመጋዝ ተሰንጥቀው በጋለ ብረት ምጣድ ላይ እንዲቆሉ አደረገ፡፡ ልጆች! በዚህ ሁሉ ስቃይ ውስጥ የእግዚአብሔር አርነትና ተራዳኢነት አልተለያቸውም ነበር፡፡ ከምጣዱ ግለት የተነሳ ቅድስት ኢየሉጣና ቅዱስ ቂርቆስ ቢሞትም እግዚአብሔር ከሞት አሥነሥቶ በንጉሡ ፊት በተአምራት እንዲቆሙ አድርጎአቸዋል፡፡ ቅዱስ ቂርቆስ በንጉሡ ፊት በቆመ ጊዜ ጸልዮ ንጉሡ ወደ እንስሳነት እንዲቀየር አድርጎታል፡፡

ልጆች! የንጉሥ መኮንን ይህን ባየ ጊዜ በሕፃኑ ቂርቆስ ላይ ተቆጥቶ ምላሱን አስቆርጦት ነበር፡፡ ነገር ግን ሁሌም ከቅዱሳን ጋር በረድኤት የማይለየው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቅዱስ ቂርቆስን የተቆረጠ ምላስ እንደቀድሞ አድርጎ አድኖለታል፡፡ ልጆች! የቅዱስ ቂርቆስን ተጋድሎ አስተዋላችሁ? ለእግዚአብሔር፣ ለሃይማኖቱ ታማኝ የሆነ ቅዱስ ነው፡፡ እናንተም ለሃይማኖታችሁ ታማኝ ትሆኑ ዘንድ ቅዱስ ቂርቆስን አርአያ ልታደርጉ ይገባችኋል፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ለአባትና እናት መታዘዝ እንዲሁም በጎ የሆነውን መንፈሳዊ ነገር ብቻ መሥራት ይጠበቅባችኋል እሺ ልጆች!

ልጆች! የቅድስት ኢየሉጣ እና የልጅዋ የቅዱስ ቂርቆስ ተጋድሎ በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ ምንም እንኳ መከራ ቢፀናባቸውም የንጉሡን ቅጣት ፈርተው ሃይማኖታቸውን አልካዱም፡፡ ንጉሡም በጽናታቸው እጅግ ስለተበሳጨ ሁለቱን ቅዱሳን በፈላ ውኃ ውስጥ እንዲጨመሩ አዘዘ፡፡ የንጉሥ ጭፍሮችም ቅድስት ኢየሉጣንና ሕፃኑ ልጅዋን ቅዱስ ቂርቆስን ወደ ፈላው ውኃ ሊጥሉአቸው ሲሉ እናቱ ቅዱስ ኢየሉጣ በፈራች ጊዜ ልጅዋ ቅዱስ ቂርቆስ ግን ‹‹እናቴ ሆይ አትፍሪ፤አናንያ ዓዛርያ፣ ሚሳኤል ከእሳት ነበልባል ያዳናቸው እግዚአብሔር እኛንም ከዚህ የፈላ ውኃ ያድነናል›› እያለ በማረጋጋት በእምነትዋ እንድትጸና ወደ እግዚአብሔር ይጸልይላት ነበር፡፡

ልጆች! ቅዱስ ቂርቆስ ያደረገውን አስተዋላችሁ? ጸሎቱንም ከጨረሰ በኋላ እናትና ልጅ ተያይዘው ከፈላው ውኃ ውስጥ ገቡ ውኃውም እንደ ውርጭ ቀዘቀዘ፤ ወታደሮችም ምንም እንዳልሆኑ ባዩ ጊዜ ስጋቸው እስኪቆራረጥ በመንኮራኩር ሲጎትቷቸው፤ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ግን ፈጥኒ ደርሶ አዳናቸው፡፡ ሁሉንም ድል ካደረጓቸው በኋላ ከእግዚአብሔርም ቃል ኪዳንን ተቀብለው በመንፈቀ ሌሊት አንገታቸውን ተቆርጠው በሰማዕትነት አርፈዋል፡፡ እስከ ሞት ድረስ ለእግዚአብሔር በመታመናቸውም የሕይወትን አክሊል ከአምላካቸው ዘንድ ተቀብለዋል፡፡

ልጆች! የቅዱስ ቂርቆስንና የቅድስት ኢየሉጣን ተጋድሎ አስተዋላችሁ? ለጌታችንና መድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ሲሉ ራሳቸውን ለመከራና ለሞት አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ እኛም በሃይማኖታችን ምክንያት መከራ ሲያጋጥመን እንደ ቅዱስ ቂርቆስ ቆራጥ ልንሆን ይገባል፡፡ ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችም እንዲበረቱ እንደ ቅዱስ ቂርቆስ ልናበረታቸው ይገባል እሺ ልጆች!

ይህን እንድናደርግም የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለየን የቅዱስ ገብርኤል፣ የቅድስት ኢየሉጣና የቅዱስ ቂርቆስ ጸሎታቸው ትጠብቀን! አሜን!

**ምንጭ፦** መጽሐፈ ስንክሳር
ድርሳነ ገብርኤል
ገድለ ቅዱስ ቂርቆስ ወኢየሉጣ

# የራበው ቢኖር በቤቱ ይብላ!

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

ቤተ ክርስቲያን የተቀደሰች ሥፍራ ነች፡፡ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ባለበት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በተለየ ቅጽር ውስጥም ክርስቲያኖች የሚመላለሱበት የራሳቸው ሥርዓት አለ፡፡ ቦታውም የተቀደሰ ነው ብሎ በማመን ለተገኘው ተግባር ሁሉ የማይውል፤ በተለያዩ ሥጋዊ ተግባራት ተጠምዶ የማይዋልበት፣ የማይታወክ ሥፍራ ማለት ነው፡፡ ሥፍራው የተለየው ለተቀደሱና መንፈሳዊ ለሆኑ ተግባራት ብቻ ነው፡፡

ለዚህ ሥፍራ ክብር ደግሞ ዋናው መሠረቱ የእግዚአብሔር ዓይኖች ዘወትር በዚህ ሥፍራ ላይ አገልግሎት በሚሰጡና በሚቀበሉ ትጉሃን ላይ በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህም ጠቢቡ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ማደሪያ ለይቶ የሠራውን ቤተ መቅደስ ‹‹ባሪያህ ወደዚህ ሥፍራ የሚጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ፥ በዚያ ስሜ ይሆናል ወዳልኸው ሥፍራ ወደዚህ ቤት ዓይኖችህ ሌሊትና ቀን የተገለጡ ይሁኑ፡፡›› (፩ኛ ነገ ፰፥ ፳፱) ብሎ ከተናገረለት ክብር በበለጠ ሕንፃ ቤተክርስቲያን የተለየ ነው፡፡

እንደተባለውም በዚህ ቅዱስ ሥፍራ ላይ የብዙዎች ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል፡፡ ለጸሎት የሚያስፈልገው ጸጥታና እርጋታም ለዚህ ሥፍራ ያስፈልገዋል፡፡ ሰዎች ሲጸልዩ የስሜት ሕዋሶቻቸውን ሁሉ የሚያውክ ከጸሎት የሚያናጥባቸው፣ ትኩረት የሚነፍጋቸው ነገር እንዲኖር አይፈቀድም፡፡ እግዚአብሔር ከጸሎተኞች ጋር ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ተግተው የሚጸልዩ የቅዱሳን መናኸሪያ ነች፡፡ ሁለትም ሦስትም ሆናችሁ በተሰበሰባችሁበት ሥፍራ እኔ በመካከላችሁ እገኛለሁ ባለው አምላካዊ ቃሉ መሠረት በዚያ የሚገኙ ትጉሃንን ሁሉ ይጎበኛልና ፲፫፥፳፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከምንም በላይ መንፈሳዊት ነች፡፡ መንፈሳዊት ስትባልም በዚያች ሥፍራ መንፈሳዊ ዓላማ ያላቸው ነገሮች ብቻ የሚደረጉባት ሥፍራ ነች ማለት ነው፡፡ ተርታ ሥጋዊ ነገሮች አይደረጉም፡፡ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን የሚፈጸሙባት ሥጋ ወደሙ የሚፈተትባት፣ ቅዳሴ ውዳሴ የሚሰማባት፣ ቃለ እግዚአብሔር የሚፈስባት የቃሉ ማዕድ የአምልኮ ሥርዓት ሁሉ የሚከወንባት የሚቀርብባት ድንቅ ሥፍራ ነች፡፡

በቅጽሯም ሁሉ ለቅዱሳን መታሰቢያ የሚሆኑ የፈውስ ቦታዎች (ጸበሉ እምነቱ…) ይገኛል፡፡ በዚህም መንፈስ ቅዱስ ብዙዎችን ይባርካል ይፈውሳል፡፡ በረድኤት በበረከትም ይቀርባቸዋል፡፡

ስለዚህ በዚህች ሥፍራ የሚደረጉ ነገሮች ሁሉ መንፈሳዊ ዓላማ ያላቸውና መንፈስ ቅዱስን የሚያስደስቱ መሆናቸውን ማጤን ይገባል፡፡

አሁን፣ አሁን ግን በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ይልቁንም በአዲስ አበባ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ቅጽሮች ውስጥ ሰዎች በማወቅም ባለማወቅም መጠለያ ሥፍራዎችን ተገን በማድረግ በሥፍራው የራሳቸውን ምግብ ሲመገቡ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬዎችን ሲጠቀሙ፣ የታሸጉ ምግቦችን ሲወስዱ፣ ለስላሳ መጠጦችን ሲጎነጩ የምናይበት አጋጣሚ እየጨመረ ነው፡፡ በተለይም ቅጽራቸው ሰፊ በሆኑ አጥቢያዎች ለዚህ መሰል ድርጊት ተጋላጭ ሆነዋል፡፡

ሰዎች መብላት መጠጣታቸው ክፉት የለውም፤ ባሕርያዊም ነው፡፡ ነገር ግን የምንበላበትን ሥፍራ መምረጥና ማወቅ አለመቻል ትዝብት ላይ ይጥላል፡፡ ከቤታችን ጀምሮ ምግብ የምንበላባቸው የተለዩ ሥፍራዎች አሉ፡፡ መጠቀም የሚገባውም በዚያ ነው፡፡ ይህ ዓይነት ተግባር ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውጪ ሊሆን ይገባል፡፡

ምእመናን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰንበት ወይም በቅዱሳን ስም በሚደረጉ ዝክሮች፣ ጽዋዕ ማኅበራት ወዘተ ለመንፈሳዊ ዓላማ ከድሆች ጋር እየተጋሩ የሚካፈሉት ፍጹም መንፈሳዊ ሆነ ሥርዓት ይፈጽማል፡፡ ካህናትም ከአገልግሎት መልስ አረፍ ብለው የተቀደሰውን ማዕድ የሚሳተፉበት የተለየ ሥፍራ ደጀ ሰላም አላቸው፡፡ በሌላ መንገድ ግን ሰዎች እንዲበሉ እንዲጠጡባቸው እንዲዝናኑባቸውም ተብለው የተለዩ ሥፍራዎች በቅጽረ ቤተክርስቲያን አይኖሩም፡፡ ይሁን እንጂ አስቀድመን በጠቀስነው ሁኔታ ግለሰቦች የራሳቸውን ምግብ የሚበሉበት አጋጣሚ እየበዛ ነው፡፡

በአንድ በኩል እነዚህ የታሸጉና የተጠቀለሉ ምግቦችን ማሸጊያና መጠቅለያ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ጥሎ መሄድ ብቻ በእጅጉ ትዝብት ላይ የሚጥል ነው፡፡

የፍራፍሬ ልጣጮችንና ፍሬዎች በየጥጋጥጉ ወድቀው መመልከትም ያስጠላል። በእነዚህ ሁኔታዎች ቅጽረ ቤተ ክርስቲያን የሚጣል ቆሻሻ እንዲታይበት ማድረጉ ተገቢነት የለውም። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ነገሮች ሽታ ስለሚፈጥሩ ለጸሎት ሥፍራ የማይገቡ ናቸው። ከምንም በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን የሚያከብር ሰው ቦታውን በዚህ ዓይነት ተግባር መጠቀም ተገቢ አይደለም።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤቱ መነገጃ እንዳትሆን ሻጭ ለዋጮችን የተቃወመው ሥጋዊ ሥራ ስለምን ተሠራበት ብሎ እንጂ ሻጭ ለዋጮች እንዳይኖሩ እንዳይሠሩም መቃወሙ አልነበረም፡ ፡ ‹‹ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በመቅደስም በሬዎችንና በጎችን ፣ርግቦችንም የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ፤ የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደስ አወጣቸው፥ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ፥ ርግብ ሻጪዎችንም፦ ይህን ከዚህ ውሰዱ፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት አላቸው።›› የሚለው ተግባሩ በአባቱ ቤት መፈጸሙን በመቃወሙ ነው። ለሁሉም ጊዜ እንዳለው ሁሉ፣ ለሁሉም ነገር ሥርዓትና ሥፍራ አለውና። (ዮሐ ፪÷ ፲፬-፲፮)

ዳግመኛም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ‹‹ የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁን አንዳችም የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን? ምን ልበላችሁ? በዚህ ነገር ላመስግናችሁን? አላመሰግናችሁም . . . ማንም የራበው ቢኖር ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ በቤቱ ይብላ። ›› (፩ኛ ቆሮ ፲፩÷ ፳፪፣ ፴፬)

አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ በመሥሪያ ቤቶች አካባቢ ባሉ አጥቢያዎች በምሳ ሰዓት ምሳ ዕቃቸውን መጠለያ ውስጥ ይዘው ገብተው ቁጭ ብለው ምሳ የሚበሉ ሠራተኞች ያጋጥማሉ። እነዚህ ሰዎች በሰዓቱ መጥተው መሳለማቸው የሚበረታታ ሆኖ ቦታውን ግን ለመመገቢያነት ማለማመዳቸው የሚመከር አይሆንም።

በሌላም በኩል የቦታውን ጽዳትና ነፋሻነት በማየት በዚያ ሥፍራ በተናጠል ወይም በቡድን መጥተው በመቀመጥ የተለያየ ምግብ ሲበሉ ይስተዋላል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ ሳይቃጠል በቅጠል ተብለው መታረም ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው። አብዛኞቹ በዚህ መንገድ ነገሮችን ለማድረግ የሚደፍሩት ባለማወቅ፣ ስለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ባለመረዳት እንደሚሆን ማሰብ ይቻላል።

ይሁን እንጂ አንዱ ሌላውን ባልንጀራውን ማስተማር፣ የሚገባውንና የማይገባውን ለይቶ ማስረዳት፣ በቁጣና በውግዘት ሳይሆን በትሕትናና በጥበብ አሳምኖ በመያዝ የሚፈታ ነው። አይተን እንዳላየ ሆነን ብናልፈው ግን ተግባሩ መስፋፋቱ ቤተ ክርስቲያንም የተርታ ሥጋዊ ነገሮች ሁሉ መፈጸሚያ እንድትሆን ይጋብዛል።

ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን ማክበር ፈሪሀ እግዚአብሔርን በውስጣችን የማሳደር ማሳያ ነው። በትንሹ የታመነ በብዙ ይሾማል እንደተባለ በእነዚህ ነገሮች ታምነን ከተገኘን ሌሎችንም ታላላቅ ሥርዓቶች ለማስከበር ረድኤተ እግዚአብሔር ይቀርብልናል።

ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም አምሳያ እንደሆነች አምነን ሰላምታ ይገባሻል እንደምንላት ሁሉ ለዚያች መንፈሳዊት ዓለም ምሳሌ ለሆነች ሥፍራ ማድረግ የሚገባንን ሳናደርግ ለሥጋችን የሚጠቅምንን ነገር በቤታችን ማድረግ የምንችለውን ለማድረግ ከተጋን ለነፍሳችን አለማድረግ አስተዛዛቢ ይሆናል።

ስለ እግዚአብሔር ክብር ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን መጠበቅ አለብን ብለን ወደ ቤቱ ስንገባ ጫማችንን የምናወልቀው ጫማችን የማያስፈልገን ሆኖ አይደለም ስለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ። ‹‹መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል።›› እንዳለ መጽሐፍ በ፩ኛ. ሳሙ ፲፫፥፳፪ እግዚአብሔርን ስለመውደድና ስለማክበር አባቶች ለሠሩት ሥርዐትና ሕግ ስለመታዘዝ እነዚህን የማይገቡ ነገሮች መሸሽ ያስፈልጋል።

አገልጋዮች ምእመናንን፣ ምእመናንም እርስ በርስ በመመካከር አጥቢያዎች በቃል ከሚሰጡት ትምህርትም በተጨማሪ በጽሑፍ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ላይ በመለጠፍ በዚያ ሥፍራ የሚታደሙትን ሁሉ ማሳሰብ ይጠበቅባቸዋል። ይህ ተግባራዊ ከሆነ ከምንወቀሳቸው ብናቀናቸው አገልግሎታችን ፍሬያማ ይሆናል፤ የቅጽረ ቤተ ክርስቲያንም ግቢ ተከብሮ ይኖራል።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# ሰዎችን በክፉ ካላማሁ ደስተኛ አልሆንም

ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች እንዴት አላችሁ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ፡፡ እጅግ የተቸገርኩበትን የራሴን ልማድ መተው ወይም መሸሽ አልቻልኩምና ችግሬን አካፍያችሁ መፍትሔ ትሰጡኝ ዘንድ ወደድኩ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ ሰዎች በተለያየ መንገድ እንደሚደሰቱ አውቃለሁ እኔ ግን ብዙ ጊዜ የምደሰተው ከሰዎች ጋር በማውራት ነው፡፡ ከሰዎች ጋር ብዙ ጉዳዮችን እያፈራረቅሁ ማውራት አዘወትራለሁ፡፡ ዝምተኛ ሰው አያስደስተኝም፡፡ ቁጥብ ሰዎችም ምርጫዬ አይደሉም፡፡ በብዙ ወሬዎች ውስጥ ደግሞ ሰዎችን ማንሣት አይቀርም፡፡ ይህ ደግሞ መልካም አለመሆኑን ብረዳም መሸሽ ግን አልቻልኩም፡፡ ከጓደኞቼ ጋር በምጫወትበት ጊዜ ሁሉ ሰዎችን ሳያነሡ ለማውራት ብሞክርም ከዚያ ለመውጣት ግን ተቸገርኩ፡፡ ሌሎች ሰዎችን ሳናነሣ እንጫወት ብለን ብዙ ጊዜ ስንሞክር ጨዋታችን እያለቀ መፋዘዝ ውስጥ  እንገባለን፡፡ ለመነቃቃት የምንሞክረው የሆኑ ሰዎችን ስም አንሥተን ስንጫወት ነው፡፡ ከመሥሪያ ቤት ሰዎች፣ ከቤተ ክርስቲያን ሰዎች፣ ከፖለቲካ ሰዎች፣ ከጎረቤቶቻችን፣ ወዘተ አንዱን ወይም ሌላውን ማንሣታችን አይቀርም፤ ታዲያ እንዴት መሸሽ እችላለሁ ምከሩኝ፡፡

ውድ ጠያቂያችን! በመጀመሪያ ውስጥዎ ያለውን ጥያቄና አለብኝ የሚሉትን ችግር  ተገንዝበው ምክር ፍለጋ ወደ ጋዜጣችን መልእክት በመላክዎ ከልብ እናመሰግናለን፡፡ የአንድ ክርስቲያናዊ መለያ ዕረፍት የሚነሣውን፣ ሕይወትን የሚጎዳ ችግር በውል ተገንዝቦ ምክሩኝ በማለት በትሑት ሰብእና መቅረብ መቻሉ ነው፡፡ አንድ ታማሚ የሚጎዳው በሕመም በመያዙ ብቻ ሳይሆን ከሕመም ለመዳን ጥረት ማድረግ ካልቻለ ነው፡፡ መንፈሳዊ ሕይወትም እክል ሊያጋጥመው ይችላል፤ እክሉን መቅረፍ የሚቻለው ግን መንፈሳዊ መፍትሔን በመሻት ነው፡፡

እርስዎም በእጅጉ እየተቸገሩበት ያለውን የሐሜት ልማድ እንዴት ልሽሽ ብለው ባቀረቡት ጥያቄ ሌሎችም በምክሩ እንደሚጠቀሙ በማመን ስለጉዳዩ እናንሣ፡፡

ክፉ ሐሜት ማለት አንድን ሰው በሌለበት፣ በማያውቅበት ሁኔታ፣ ለሰዎች የተዛባ፣ ሐሰተኛ፣ ሊጎዳው የሚችል መረጃ መስጠት ነው፡፡ ሰውን በአሉታ ለማንሣት የሚያደፋፍረው ፍቅር ማጣት ነው፡፡ ፍቅር ያለው ሰው ወንደሙ ቢበድል እንኳን በደሉን ይሸፍናል፣ ከበደል እንዲወጣ ይጸለይታል እንጂ በሰውም በእግዚአብሔርም ፊት ሊያሳጣው አይነሣም፡፡ ሐዋርያው እንዲህ ይላል ‹‹ፍቅር የበደልን ብዛት ይሸፍናል›› (፩ኛ ጴጥ ፬፥ ፰)

ፍቅር ሌላው ቢያጠፋም እንኳን እንድንታገሰው እንጂ እንድንበቀለው፣ እንድንፈርድበትም አያነሣሣም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ፍቅር ያስታግሳል›› ያለውም ለዚህ ነው፡፡ ሐሜት ሰውን በሌለበት ያልዋለበትን፣ ያልሠራውን ሠራ ወይም አደረገ እያሉ ለሰዎች ማውራት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ሐሜት የፍቅር መጉደል ዋነኛ ማሳያ ነው፡፡

ሐሜት በክርስትና ሕይወት ውስጥ ጎጂ በመሆኑ መወገድ ያለበት ነገር ነው፡፡ ሐዋርያው ‹‹እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኰልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንዓትንም ሐሜትንም ሁሉ አስወግዳችሁ፥...›› (፩ኛ ጴጥ. ፪፥፩) ማለቱ ሐሜት የታወቀ ኃጢአት መሆኑን ያሳያል፡፡

ውድ ጠያቂያችን!  እርስዎም ገባሁበት ያሉት ልማድ ከዚህ አንጻር የሚታይ እስከሆነ ድረስ የኃጢአት ሥራ መሆኑን በውል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እርስዎ እንዳሉትም ከሰዎች ጋር በሚሰባሰቡበት ጊዜ የደስታችሁ ምንጭ ወሬ ሆኖ ሳለ በዚያ ውስጥ ደግሞ ማጣፈጫው ሰዎችን በሌሉበት በአሉታ ማንሣት ከሆነ እጅግ ለከፋ ኃጢአት ይዳርጋል፡፡ ይህን ልማድ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ የደስታ ምንጭ እስከመሆን መድረሱ ነው፡፡ ሰዎች ሰውን  በአሉታ ሐሜት ካላነሡ ለድባቴ የሚጋለጡ ከሆነ በኃጢአት መደሰትን የኑሮአቸው ማጣፈጫ አድርገውታል ማለት ነው፡፡

በእርስዎ በኩል ያለው መልካሙ ነገር ችግሩ ፈተና ሆኖ እንደያዘዎት መረዳትዎ ነው፡፡ ከዚህ ለመላቀቅ ያለዎት ፍላጎትም በልዩ ልዩ መንፈሳዊ እርምጃዎች ከታገዘ ሊሳካ የሚችል ነው፡፡ ችግሩ ግን የብዙ ሰዎች ሲሆን ባለማስተዋል እንደ መልካም ነገር ተቆጥሮ እንደልብስ ታጥቆት የሚዞር መብዛቱ ነው፡፡ ሐሜት የብዙ ሰዎች ልማድ ሲሆንና ሲዘወተር መልካም ሆኖ መታየት ይጀምራል፡፡

ስለዚህ ሰዎች ለመብላት፣ ለመዝናናት፣ ለሥራም፣ በቤተሰብ ውስጥም ሲሰበሰቡ የሰዎችን ስም እያፈራረቁ በማማት ጨዋታቸውን ያደመቁ ይመስላቸዋል፡፡ ስለዚህ ከጎረቤት ጀምረው እስከ ንጉሡና ጳጳሱ ድረስ በማማት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉ ሰዎች ቀላል ቁጥር እንደሌላቸው ይታሰባል፡፡

ውድ ጠያቂያችን በእርስዎ በኩል ለጉዳዩ ትኩረት መስጠትዎና እንዴት ልሸሸው ብለው መቅረብዎ ሐሜትን ለማጥፋት አቅም መፍጠር መጀመርዎን ያሳያል፡፡ ከምንም በላይ ግን የሚከተሉትን ነጥቦች ተከትለው ሕይወትዎን ለማነጽ ቢሞክሩ የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ያስችላል ብለን እናምናለን፡፡

1ኛው. ሐሜትን ለመሸሽ መጀመሪያ የሚያስፈልገው ዓላማ ያለው አዋዋል ይዞ መገኘት ነው፡፡ ሰዎች ውሎአቸው ትርጉም ባለው መንገድ ማሳለፍ ከፈለጉ ከዚህ የሚሸሹበትን አቅም ያገኛሉ፡፡ ከማን ጋር መዋል እንዳለብን፣ አብረን ከምንውለው ሰው ጋር ምን ጠቃሚ ነገር እንዳርጋለን፣ እናወራለን ብሎ በውል የውሎን አቅጣጫ በመበየን ሥርዓት ያለው አዋዋል እንዲኖረን ያስችላል፡፡ ማንንም ለምንም ምክንያት ማግኘት ያልተፈለገ፣ ያልታቀደ የሚጎዳም ነገር ለማውራትና ለማድረግ ይዳርጋል፡፡ በምክንያት የሚያገኙትን ሰው ምን እንደሚያወሩት ያውቃሉ፣ ለምን

ያህል ጊዜ አብሮ ለማሳለፍ እንደሚፈልጉም ያውቃሉ፡፡ ስለዚህም በምን መጠን ምን እንደሚያወሩም ተረድተዋል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ከእርስዎ የሚጠበቀው የሚያወሩትን ወሬ ይዞታ ቀድመው ጠቃሚ፣ ከሐሜት የጸዳ እንዲሆን ማዘጋጀት ነው፡፡

2ኛው. ከዚሁ ነጥብ ጋር የሚያያዘው ዓላማ ባለው መንገድ ውሎውን የሚያቅድ ሰው ጓደኛ መምረጥ ላይ ይጠነቀቃል፡፡ ጓደኛን በጥንቃቄ መምረጥ ከሀሜት ለመጽዳት ይበጃል፡፡ ከማውራት ይልቅ መሥራትን የሚመርጥ፣ መሥራትን ሲመርጥ ደግሞ ያገኘ የአጣውን ለማውራት ከማይፈቅድ ሰው ጋር ጓደኛ ለመሆን ይቻላል፡፡ ሐሜትን የማይሻ ጓደኛ በእርሱ ብቻ ሳይሆን በእርስዎም ውስጥ በስሕተት እንኳን ወደ ሐሜት የሚያዘነብል ጨዋታ ቢነሣ እንኳ ለማረም ያስችላል፡፡ እርስዎ በጥያቄዎ እንደጠቀሱት ዓይነት ሰው ማለትም ቁጥብ ሰው ከመጥላት ይልቅ ምርጫዎ ቢያደርጉም ይመከራሉ፡፡

3ኛው. ደጋግሞ ማመን የሚያስፈልገው ሐሜት ኃጢአት መሆኑን ነው፡፡ እስኪ ጠቢቡ ሰሎሞን ሐሜተኛን የሚወቅስበት የሚገስጽበትን መልእክቶቹን እናስታውስ ‹‹ዞዋሪ ሐሜተኛ ምሥጢርን ይገልጣል፤ ከንፈሩን የሚያሞጠሙጥ ሰውን አትገናኘው፡፡›› (ምሳ. ፳፥፲፱) ደግመኛም እንዲህ አለ ‹‹የሰሜን ነፋስ ወጀብ ያመጣል፤ ሐሜተኛ ምላስም የሰውን ፊት ያስቈጣል፡፡›› (ምሳ. ፳፭፥፳፫) ሁሉም ሰው ማወቅ ያለበት በምንናገረው ነገር መልካም ፍሬ ማፍራት እንድምንችል ሁሉ ክፉ ፍሬም ማፍራት እንዳለ ነው፡፡ ‹‹ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው፤ የሚወድዱአትም ፍሬዋን ይበላሉ፡፡›› (ምሳ ፲፰÷፳፩)

ክፉ ፍሬ ግን በእግዚአብሔር የማይወደድ የኃጢአት ፍሬ በመሆኑ ጠቢቡ እንዳለው ሕይወትን ሳይሆን ሞትን የሚያመጣ ይሆናል፡፡በተለይ ሀሜት ባልተገደድንበት ሁኔታ በራሳችን ፈቃድ ስለሌሎች በማውራት የምንገባበት መከራ ነው፡፡ ሐዋርያው ግን ‹‹ከእናንተ ማንም … በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል፤››(፩ኛ ጴጥሮ ፬÷፲፭) ብሎናል፡፡

ውድ ጠያቂያችን ሐሜት የሚመነጨው ከእርስዎ ብቻ ሳይሆን ይችላል፡፡ በግብረ መልስ በመሳተፍ ግን የሐሜቱ አካል መሆን ጉዳት አለው፡፡ ስለ ሰዎች ለመስማት ጆሮአችንን ማቀብቀብ ፈተና ያመጣብናል ይልቁንም ከሐሜት ለመዳን ጆሮአችንም ሐሜትን እንዳይሰማ በመቀጠብም ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የውስጥ የውጪም ሰላም ይገኛል፡፡ መጽሐፍ እንዲህ ይላል ‹‹እንጨት ባለቀ ጊዜ እሳት ይጠፋል፤ ጆሮ ጠቢ በሌለበትም ዘንድ ጠብ ጸጥ ይላል፡፡›› (ምሳ. ፳፮፥ ፳)፡፡

ቢያንስ ሌሎች የሐሜትን ነገር ሲያመጡ በተለያዩ መንገዶች እንዳይበረታቱ ማድረግ ይቻላል፡፡ የሚያወሩትን ነገር በምን እንዳረጋገጡ በመጠየቅ፣ ስለሚያነሡት ሰው ማንሣታቸው ለምን እንደሚጠቅም በመጠየቅ ወዘተርፈ ሐሜቱን እንዲያቆሙ ማድረግ ይቻላል፡፡

4ኛው. ወሳኝ መላ ግን አንደበትን ለዘወተር የሚጠቅም፣ መንፈሳዊና ለጽድቅ አገልግሎት እንዲነሣሣ ማንቃት ነው፡፡ ከምናገኘው ሰው ጋር በራሳችን ወይም አብሮን ባለ ሰው ጉዳይ ላይ ለመተራረም ማውራት አስፈላጊ ነው፡፡ ያም ቢሆን ጠቃሚ ወሬ መያዛችንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ከዚያ ከተሻገረም የመንፈስ ፍሬን ለማፍራት የሚጠቅም እንዲሆን መትጋት ነው፡፡ በምናደንቀው ቅዱስ ቃል፣ በምንማርበት መልካም ምክር፣ ልንከተለው በሚገባ መልካም ፈለግ፣ በሚያንጸን ታሪክ፣ ለቤተሰባችን በሚጠቅም ጥበብ ወዘተ መወያየት ራስንና ባልንጀራን ከሀሜት ለመጠበቅ ይረዳል፡፡

ውድ ጠያቂያችን! ከምንም በላይ ግን አሳሳቢው ነገር ሐሜት የደስታ ምንጭ ሆኖ ከሕይወት ጋር መተሳሰሩ ብርቱ ፈተና ነው። ስለዚህ በቀላሉ ለመንቀል ባለመቻልዎ ሊገረሙ ይገባም፡፡ ጥረት ማድረግ ግን መልካም ነው፡፡ በዚህ ጥረት ውስጥ ድብርት(ድባቴ) ሊመጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ በቃለ እግዚአብሔር የበለጠ ለመበርታት መጣር ያስፈልጋል፡፡ ጸሎት ግን ከሁሉም በላይ አስፈላጊ ነው፡፡ መክንያቱም የአንድበት ኃጢአት ሰዎች አንደሚያስቡት ቀላል አይደለም፤ ለመላቀቅም የእግዚአብሔር ረድኤት ያስፈልገናል፡፡ የአንደበትን የዐመጽ መንገድ ሐዋርያው እንዲህ ገልጾልናል፡፡

‹‹እነሆ፥ ፈረሶች ይታዘዙልን ዘንድ ልጓም በአፋቸው ውስጥ እናገባለን፥ ሥጋቸውንም ሁሉ እንመራለን፡፡ እነሆ፥ መርከቦች ደግሞ ይህን ያህል ታላቅ ቢሆኑ በዐውሎ ነፋስም ቢነዱ፥ የመሪ ፈቃድ ወደሚወደው ስፍራ እጅግ ታናሽ በሆነ መቅዘፊያ ይመራሉ፡፡ እንዲሁም አንደበት ደግሞ ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል፡፡ እነሆ፥ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ትልቅ ጫካ ያቃጥላል፡፡ አንደበትም እሳት ነው፡፡ አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃጠላል፡፡ የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል፥ ደግሞ ተገርቶአል፤ ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም፤›› (ያዕቆ ፫ ፥ ፫-፱)

ባጠቃላይ ሐሜት ወይም የሐሜት ልምምድ ተናጋሪውን ራሱን ከመጉዳቱም በላይ የሚታማውንም ሰው ይበልጥ እንደሚጎዳ ጭምር በውል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ጠቢቡ ሶሎሞን ‹‹ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው፤ የሚወዱአትም ፍሬዋን ይበላሉ፡፡ (ምሳ. ፲፰፥፳፩) እንዳለው በገዛ እጃችን ራሳችንን ወደ ሲኦል የምንከትበት አሊያም መንግስተ ሰማያት ወራሾች የምንሆንበት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው የሰዎችን ስም በከንቱ ከማንሳት ባለፈ በሰዎች መካከል ጠብን ለመዝራት፣ መከፋፈልን ለማምጣት፣ መጠራጠርን ለማስፋፋት ትልቁ መግቢያ በር ሐሜት መሆኑን አሁንም ጠቢቡ ‹‹ የሰሜን ነፋስ ወጀብን ያመጣል፤ ሐሜተኛ ምላስም የሰውን ፊት ያስቆጣል፡፡ (ምሳ.፳፭፥፳፫) በማለት የሐሜትን አደገኛት አስረግጦ ይነግረናል፡፡ ስለዚህ ከዚህ ብርቱ ወጥመድ ለመላቀቅ የምንችለው በእግዚአብሔር ረድኤት መሆኑንም ተገንዝበው በጸሎትም ይበርቱ እንላለን፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*